# አዲስ ዘመን

እናድ

ረቡዕ

83ኛ ዓመት ቁጥር 086 ኅዳር 26 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!














ፎቶ፡ ገዛኸ ገብሬ

# "ኢትዮጵያውያን ተባብረን ለሰላም ዘብ በመቆም አንድነታችንን ማጠናከር ይገባናል"

**- ሼህ ሐጂ ኢብራሂም ቱፋ**
**የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት**

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያውያን ተባብረን ለሰላም ዘብ በመቆም አንድነታችንን ማጠናከር ይገባናል ሲሉ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሼህ ሐጂ ኢብራሂም ቱፋ ገለጹ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እና የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ የሙስሊሙ ማህብረሰብ የተለያዩ ጥያቄዎች ምላሽ እንዲያገኙ ላበረከቱት አስተዋጽኦ የምስጋና ሽልማት ተበርክቶላቸዋል።

"ቀጣይ ምዕራፍ ለሁለንተናዊ ለውጥ" በሚል መሪ ሃሳብ የሠላምና የምስጋና ፕሮግራም በሚሊኒየም አዳራሽ ትናንትና ተካሂዷል፡፡

በመድረኩ የተገኙት የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሼህ ሐጂ ኢብራሂም ቱፋ፤ ሰላም በሰዎች መካከል የሚፈጠርን ግጭት በማስወገድ መልካም እሴቶች

"ኢትዮጵያውያን... ወደ ገጽ4 ዞሯል



# "ኢትዮጵያ በአፍሪካ የሩሲያ አስተማማኝ አጋር ናት"

- የሩሲያ ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ከሩሲያ ጋር 125 ዓመታትን አብራ የቆየችና በአፍሪካም የሩሲያ አስተማማኝ አጋር ናት ሲሉ ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን ተናገሩ።

ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን ከተለያዩ ሀገራት አዲስ የተሾሙ 21 የውጭ ሀገራት አምባሳደሮች የሹመት ደብዳቤን በታላቁ

"ኢትዮጵያ በአፍሪካ... ወደ ገጽ4 ዞሯል



# ያልተጠቀምንበት የቆዳ ሀብታችን

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**

ኢትዮጵያ በቀንድ ከብት ሀብቷ ከአፍሪካ አንደኛ ከዓለም ስምንተኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች። የቆዳ ኢንዱስትሪዋም ከ90 ዓመታት በላይ እድሜን ያስቆጠረ ነው። ይሁን እንጂ ሀገራችን ከዘርፉ እያገኘች ያለችው ገቢ ካላት የቀንድ ከብት ሀብት ጋር የሚነጻጸር አልሆነም። ኢንዱስትሪውም ቢሆን የእድሜውን ያህል አላደገም።

ከራስ አልፎ ለሌላው መትረፍ የሚችል የቆዳ ግብዓት እያለን ጥራት ያለው ቆዳና ሌጦ ማዘጋጀት ባለመቻላችን የቆዳ ውጤቶች አምራች ኢንዱስትሪዎቻችንም በውጭ ምንዛሪ ቆዳን ከውጭ እያስገቡ ለመጠቀም መገደዳቸውንም ሲናገሩ ይሰማሉ። ለመሆኑ ከቡና ቀጥሎ ለሀገራችን ከፍተኛ ገቢ ያስገኝ የነበረው የቆዳና ሌጦ ዘርፍ ለማሽቆልቆል የዳረገው ምንድነው? ቀድሞ ወደነበረበት ደረጃ ለመመለስና በእጃችን ያለውን ይህን ሀብት ለመጠቀም ምን እየተሠራ ነው? ዘርፉ ለመነሳት የየትኞቹን

ያልተጠቀምንበት... ወደ ገጽ4 ዞሯል

# የባሌ ተራሮች

## የቱሪዝም ሀብት ለዘላቂ ልማት እንዲውል ሰፊ ድጋፍ ያስፈልጋል

ገጽ 4







# ዩኒቨርሲቲው አዲስ ተማሪዎቹን በመቀበል ትምህርት መስጠት የሚያስችለውን በቂ ዝግጅት አድርጓል

**መዓዛ ማሞ**



አዲስ አበባ፡- አዲስ የተመደቡ ተማሪዎችን በመቀበል ትምህርት መስጠት የሚያስችለውን በቂ ዝግጅት ማድረጉን የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ገለጸ። በ2016 ዓ.ም በዩኒቨርሲቲው ከተመደቡት አንድ ሺ 574 ተማሪዎች መካከል 90 በመቶዎቹ በጊቢው ተገኝተው ሪፖርት አድርገዋል።

የዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዚዳንት ከማል ኢብራሂም (ዶ/ር) ትናንት ለጋዜጠኞች እንደገለጹት፤ ዩኒቨርሲቲው ተማሪዎቹን ተቀብሎ ትምህርት ለመጀመር በቂ ዝግጅት አድርጓል።

ዩኒቨርሲቲው በ2016 ዓ.ም የተመደቡለትን አዲስ ተማሪዎች ቅበላ በከፊል ማጠናቀቁን የጠቆሙት ዶክተር ከማል፤ ከተመደቡት አንድ ሺ 574 አዲስ ተማሪዎች መካከል 90 በመቶዎቹ በዩኒቨርሲቲው ተገኝተው ሪፖርት ማድረጋቸውን አስታውቀዋል።

ተማሪዎቹን ለመቀበል ቀደም ብሎ ዝግጅቶች ሲደረጉ መቆየታቸውን አስታውሰው፤ የተለያዩ የአስተዳደር ክፍሎች የተካተቱበት ኮሚቴ ተዋቅሮ ሲሠራ መቆየቱን አመላክተዋል።

ተማሪዎቹ ወደ ዩኒቨርሲቲው ከመግባታቸው አስቀድሞ የተመደቡበትን ማደሪያ ክፍልና የዩኒቨርሲቲ መታወቂያ ቁጥራቸውን እንዲያውቁት መደረጉን ተናግረው፤ ዝግጅቱ ተማሪዎቹ መደናገር ሳይፈጠርባቸው በጊቢው የተሻለ አገልግሎት እንዲያገኙ ጠቅሟል ሲሉ አብራርተዋል።

ከተለያዩ የሀገሪቷ አካባቢዎች ወደ ዩኒቨርሲቲው ለሚመጡ ተማሪዎች ከመናኸሪያዎች ወደ ዩኒቨርሲቲ የሚያመላልሱ ተሽከርካሪዎችን በመመደብ ተማሪዎቹ እንዳይጉላሉ መደረጉንም አስረድተዋል።

ዩኒቨርሲቲው ነባር ተማሪዎችን ከስድስት ሳምንታት በፊት ጀምሮ በመቀበል ትምህርት እየሰጠ መሆኑን ገልጸው፤ አዲስ ለገቡት ተማሪዎች አስቀድሞ መምህራን መመደቡንና ትምህርት ለመጀመር በቂ ዝግጅት መደረጉን ጠቁመዋል።

ዩኒቨርሲቲው "ዜሮ ዋን ዜሮ ዋን" ከተሰኘ ድርጅት ጋር የአጋርነት ፊርማ መፈራረሙን የጠቆሙት ዶክተር ከማል፤ አጋር ድርጅቱ ተማሪዎቹን በስብዕና ግንባታ ላይ እንደሚያግዛቸው አመላክተዋል።

በዩኒቨርሲቲው ትምህርቷን ለመከታተል ከሐረር የመጣችው ተማሪ ማሕሌት አለማየሁ፤ ወደ ዩኒቨርሲቲው ከመምጣቷ በፊት ስለዩኒቨርሲቲው የሰማችው ነገር ስጋት እንደፈጠረባትና ወደ ዩኒቨርሲቲው ከደረሰች በኋላ ግን ፈጽሞ የተለየ እንክብካቤ እንዳጋጠማት ለኢፕድ ገልጻለች።

ማደሪያ ክፍሏንና የዩኒቨርሲቲ መታወቂያ ቁጥሯንም አስቀድማ ማወቋ በዩኒቨርሲቲው ስትደርስ ግራ መጋባት እንዳይፈጠርባት እንዳገዛት የተናገረችው ተማሪዋ፤ በዩኒቨርሲቲ ቆይታዬ "ኮምፒውተር ኢንጂነሪንግ" ወይም "መካኒካል ኢንጂነሪንግ" ዘርፍ ለማጥናት ሃሳብ አለኝ፤ ለዚህም ይረዳኝ ዘንድ የተደረገልኝ አቀባበል ጠንክሬ እንድሠራ የሞራል ስንቅ ሆኖኛል ብላለች።

ሌላኛው በዩኒቨርሲቲው የተመደበው የአዲስ አበባ ነዋሪው ተማሪ ናትናኤል በላይ በበኩሉ፤ በዩኒቨርሲቲው የተደረገለት አቀባበል መልካም ስሜት እንደፈጠረበት ገልጿል።

መልካም አቀባበሉ መጀመሪያ ላይ የሚኖረውን የዩኒቨርሲቲ ፍራቻ እንዳስቀረለት ተናግሮ፤ "ኤሌክትሮ መካኒካል" ወይም "ማይኒንግ" ዲፓርትመንት ገብቶ ትምህርቱን የመከታተል ፍላጎት እንዳለውና ለዚህም በቂ የሥነልቦና ዝግጅት ማድረጉን አስረድቷል።

አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ አዲስ ገቢ ተማሪዎችን ከህዳር 23 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ መቀበሉ ይታወቃል። ተማሪዎች ስለዩኒቨርሲቲው ግንዛቤ እንዲኖራቸው የትውውቅ መርሃ ግብር የተደረገላቸው ሲሆን፤ የቤተ-ሙከራ ጉብኝት፣ የትምህርት ክፍሎች ፣ ከአገልግሎት ሰጪ ቢሮዎችን ጎብኝተዋል።



# ሁለት ሚሊዮን ሀገር በቀል ችግኞችን እያዘጋጀ ነው

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በ2016 ዓ.ም ለሚከናወኑ የችግኝ ተከላ መርሃ-ግብሮች አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሀገር በቀል ችግኞችን እያዘጋጀ መሆኑን የጉለሌ እጽዋት ማዕከል አስታወቀ፡፡

የማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር ጉተማ ሞረዳ (ኢ/ር) በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በ2016 ዓ.ም የሚተከሉ አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሀገር በቀል ችግኞች በማዕከሉ እየተዘጋጁ ይገኛል።

ማዕከሉ ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ የሀገር በቀል ዕጽዋት ችግኞችን አፍልቶ ለተለያዩ አካላት ሲያከፋፍል ቆይቷል ያሉት ኢንጂነር ጉተማ፤ ካለፉት ሶስት ዓመታት ወዲህ በየዓመቱ አንድ ሚሊዮን ሀገር በቀል ዕጽዋት ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ማከፋፈሉን ገልጸዋል።

በአሁኑ ወቅት እየተዘጋጁ የሚገኙ ችግኞች በአዲስ አበባ ለሚገኙ ሁሉም ክፍለ ከተሞች የአረንጓዴ ልማትና ውበት ቢሮ እንዲሁም ድጋፍ ለሚሹ የፌዴራልና ሌሎች ተቋማት እንደሚከፋፈል አስታውቀዋል፡፡

ሀገር በቀል ዕጽዋትን ከመጥፋት ለመታደግ እንክብካቤ ማድረግ እንዲሁም የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ዕጽዋቱን የማፍላትና የማባዛት ተግባር እየተከናወነ መሆኑን ኢንጂነር ጉተማ አስረድተዋል።

ችግኞቹን ለማፍላት የተደራጁ ማህበራት መኖራቸውን አመላክተው፤ ማዕከሉ ሀገር በቀል ዕጽዋትን ከመጥፋት ከመታደግ ጎን ለጎን ለዜጎች የሥራ ዕድል እየፈጠረ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

እንደ ኢንጂነር ጉተማ ገለጻ፤ ሀገር በቀል ዕጽዋቱ የአፈር ለምነት ከመጠበቅ፣ አእዋፋትና እንስሳት በደን እጦት ምክንያት እንዳይሰደዱ ከማድረግና ሥነ-ምህዳሩን ከማሳደግ አኳያ የተሻለ ጠቀሜታ አላቸው፡፡

የማዕከሉ ዋና ዓላማ ሀገር በቀል ዕጽዋትን ከጥፋት መታደግ ነው ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በተጨማሪም በማዕከሉ የምርምር ሥራዎች እንዲሚሠሩ ገልጸዋል፡፡

የሚተከሉ ችግኞች ለመዲናዋ ተስማሚ እንዲሁም መሠረተ ልማት በማይጎዳ መልኩ እንዲሆን ለማስቻል በአጋር አካላት በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና ከዲላ ዩኒቨርሲቲ ጋር በጋራ በመሆን ጥናት ተጠንቶ መመሪያ መዘጋጀቱን አስታውቀዋል።

በማዕከሉ እስካሁን በተሰሩ የምርምር ሥራዎች ሀገር በቀል ዕጽዋትን በተሻለ መንገድ ማባዛት እንደሚቻል የመለየት ሥራ ተከናውኗል ብለዋል።

የአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖን ለመቀነስና ለነዋሪው ተስማሚ የሆነ ከተማ ለመፍጠር እንዲሁም ጤናማና ምርታማ ማህበረሰብ ለመፍጠር ሀገር በቀል እጽዋትን ተንከባክቦ ለትውልድ ማስተላለፍ ችላ የማይሉት ተግባር መሆናቸውን ኢንጂነር ጉተማ አስታውሰዋል፡፡

በተጨማሪም ሁሉም ዜጋ ሀገር በቀል ዕጽዋትን ለማፍላት የሚከፈለው ዋጋ ትልቅ መሆኑን በመገንዘብ ለተተከሉ ችግኞች ድጋፍና እንክብካቤ እንዲያደርግ ጥሪ አቅርበዋል።

# በህብረት ሥራ ማህበራቱ አማካኝነት ከ8 ሚሊዮን በላይ ዜጎች የፋይናንስ ተጠቃሚ ሆነዋል

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**



አዲስ አበባ፡- በገንዘብ ቁጠባና ብድር ህብረት ሥራ ማህበራት አማካኝነት ከስምንት ሚሊዮን በላይ ዜጎች የፋይናንስ ተጠቃሚ መሆናቸውን የኢትዮጵያ ህብረት ሥራ ኮሚሽን አስታወቀ።

በኮሚሽኑ የፋይናንስ ህብረት ሥራ ልማት መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ብርሃኑ ዱፌራ ህዳር 27 ቀን የሚከበረውን ዓለም አቀፍ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ህብረት ሥራ ቀን አስመልክቶ በሰጡት መግለጫ፤ በሀገሪቱ ከ23 ሺህ በላይ መሠረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ህብረት ሥራ ማህበራትና 128 ዩኒየኖችና እንዲሁም ሁለት ፌዴሬሽኖች አገልግሎት እየሰጡ መሆኑንና በዚህም ከስምንት ሚሊዮን በላይ ዜጎች አገልግሎት እያገኙ መሆናቸውን ተናግረዋል።

ማህበራቱ እየሰጡ ያለው የብድርም ሆነ የቁጠባ አገልግሎት ከሌሎች የፋይናንስ አንጻር ሂደቱ ቀላልና የህብረተሰቡን ነባራዊ ሁኔታ ከግምት ያስገባ መሆኑን አስረድተዋል።

የብድር ማስያዣ ዋስትና ዝቅተኛና ማህበረሰቡ በቀላሉ ሊያገኝ የሚችለውም መሆኑን አመላክተው፤ በዚህም በኢኮኖሚ አቅም በዝቅተኛ ደረጃ ያሉትን ሴቶችና ወጣቶችን የበለጠ ተጠቃሚ እያደረጉ መሆኑን ገልጸዋል።

ማህበራቱ እስካሁን ከ50 ቢሊዮን ብር በላይ ቁጠባ በማሰባሰብ ከ700 ሺህ በላይ ለሚሆኑ አባላት በየዓመቱ ከ 15 ቢሊዮን ብር በላይ ብድር እያቀረቡ ይገኛል ሲሉ አስረድተዋል።

የህብረት ሥራ ማህበራቱ የ2015 ዓ.ም እቅድ አፈጻጸም ብቻ ሲታይ ከአንድ ሚሊዮን በላይ ለሚሆኑ ዜጎች ከ 19 ቢሊዮን ብር በላይ አበድረዋል፤ ከዚህ ውስጥ ከ50 በመቶ በላይ የሚሆኑት ሴቶች ናቸው ብለዋል።

እስከ 1994 ዓ.ም ድረስ የህብረት ሥራ ማህበራት ትኩረታቸውን በከተሞች አድርገው ሲሠሩ የነበረ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት በከፍተኛ ደረጃ በገጠሩ ክፍል በስፋት እየሠሩ መሆኑን ጠቁመዋል።

በአሁኑ ወቅት በገጠራማ አካባቢዎች ከ90 በመቶ በላይ የሚሆነው የብድር አገልግሎት የሚቀርበው ለግብርናና ከግብርና ጋር ለተያያዙ ግብዓቶችና ቴክኖሎጂዎች መሆኑን አስታውቀዋል።

በተጨማሪም የህብረት ሥራ ማህበራቱ የፋይናንስ አገልግሎቱ የህብረተሰቡን አኗኗር፤ ባህልና እምነት የተከተለ በመሆኑ ብዙሃኑን ተጠቃሚ እያደረገ ይገኛል ብለዋል።

ዜና



ዶክተር ሂሩት ካሳው

# የመዲናዋን የቱሪዝም መዳረሻዎች የማስተዋወቁ ተግባር ተጠናክሮ ይቀጥላል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- የመዲናዋን የቱሪዝም መዳረሻዎች ለሀገር ውስጥና ለውጭ ጎብኚዎች የማስተዋወቁ ተግባር ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ  የአዲስ አበባ ባህል ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ።

በዓለም 44 እና በኢትዮጵያ 36ኛ ጊዜ "ቱሪዝም ለአረንጓዴ ልማት አረንጓዴ ልማት ለቱሪዝም" በሚል መሪ ሃሳብ የተካሄደው የቱሪዝም ቀን የማጠቃለያ መርሃ-ግብር ሰሞኑን ተካሂዷል።

የአዲስ አበባ ባህል ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ሃላፊ ሂሩት ካሳው (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ የመዲናዋን የቱሪዝም መዳረሻዎች ዓመቱን ሙሉ ለሀገር ውስጥና ለውጭ ጎብኚዎች የማስተዋወቅ ተግባር ተጠናክሮ መቀጠል አለበት።

በመዲናዋ የዓለም ቱሪዝም ቀን ከመስከረም ወር ጀምሮ በልዩ ልዩ ተግባራት ሲከበር ቆይቷል ያሉት ዶክተር ሂሩት የመዲናዋን የቱሪዝም መዳረሻዎች ለማስተዋወቅ ሚስ ቱሪዝም አዲስ አበባ ተመርጣለች ብለዋል።

አዲስ አበባ የብሄር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች መገኛና የአፍሪካ መዲና መሆኑዋን ጠቅሰው በመዲናዋ ሁሉንም አካታች የሆነ የቱሪዝም እንቅስቃሴ መካሄዱን አመላክተዋል።

የአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ኃፍታይ ገብረእግዚአብሔር በበኩላቸው፤ የዓለም ቱሪዝም ቀን መከበር የከተማዋን የቱሪዝም ሀብት ለማህበረሱ ግንዛቤ መፍጠር አስችሏል።

የቱሪዝም ቀንን ምክንያት በማድረግ 10 ዋና ዋና ተግባራት ሲከወኑ መቆየታቸውን የገለጹት ኃላፊው አቶ ኃፍታይ፤ የደም ልገሳ፣ ሲምፖዚየም፣ ፓናል ውይይት፣ የጎዳና ላይ ትርዒት፣ ችግኞችን የመንከባከብ ሥራዎችን ጨምሮ የእግር ጉዞና በሲዳማ ክልል ጉብኝት ተካሂደዋል ብለዋል።

በመርሃግብሩ የከተማዋን የቱሪዝም ሀብት ለማህበረሱ ግንዛቤ መፍጠር መቻሉን ጠቅሰው፤ በተለይም የሀገር ውስጥ ጎብኚዎችን ባህል ለማሳደግ የሚያስችሉ ተግባራት መከናወናቸውን ገልጸዋል። በሚስ ቱሪዝም አዲስ አበባ 2016 አማካኝነት በተለያዩ ጉባዔዎች ላይ በመገኘት የከተማዋን የቱሪዝም ሀብት የማስተዋወቅ ሥራ እንደሚሠራ ጠቁመው፤ የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎችን በማስተዋወቅ የገፅታ ግንባታ የሚሠራ መሆኑን አስረድተዋል።

የአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ከመስከረም 2016 ዓ.ም ጀምሮ "ቱሪዝም ለአረንጓዴ ልማት - አረንጓዴ ልማት ለቱሪዝም" በሚል መሪ ሃሳብ በዓለም  ለ44ኛ በኢትዮጵያ ለ36 ጊዜ የተከበረውን የቱሪዝም ቀን በተለያዩ ሁነቶች ማክበሩ ይታወሳል።

# "ከተማ አስተዳደሩ የፀረ-ሙስና ትግሉን ተቋማዊ አድርጎ ተጨባጭ ሥራዎችን እየሠራ ነው"

- የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ

**ዳግማዊት አበበ**



አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በከተማ ደረጃ የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በማቋቋም የፀረ-ሙስና ትግሉን ተቋማዊ አድርጎ ተጨባጭ ሥራዎችን በመሥራት ላይ ይገኛል ሲሉ  የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ተናገሩ።

በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ20ኛ ጊዜ "ሙስና የጋራ ጠላታችን ነው በሕብረት እንታገል" በሚል መሪ ሃሳብ የፀረ-ሙስና ቀን እየተከበረ ሲሆን በአዲስ አበባ ከተማ ደረጃም በተለያዩ ፕሮግራሞች ሲከበር ቆይቶ በትናንትናው ዕለት የማጠቃለያ መድረክ ተከናውኗል።

በማጠቃለያ መድረኩ ላይ የተገኙት ከንቲባ አዳነች አቤቤ እንደገለጹት፤ ሙስና ላይ የሚደረገው ትግል የታይታ መሆን የለበትም የእውነት ለውጥ የሚያመጣ መሆን አለበት።

በዚህም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በከተማ ደረጃ የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በማቋቋም የፀረ-ሙስና ትግሉን ተቋማዊ አድርጎ ተጨባጭ ሥራዎችን በመሥራት ላይ ይገኛል ብለዋል።

ሙስና የአንድን ሀገር እድገት በእጅጉ የሚጎዳ፣ ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል እንዳይኖር የሚያደርግ እና ሀገር ገቢዋን በአግባቡ እንዳትሰበስብ እንቅፋት የሚፈጥር ነው ያሉት ከንቲባዋ፤ ከዚህ በተጨማሪ ዘርፈ ብዙ ጉዳቶችን የሚያደርሰውን ሙስናን ለመከላከል የሚደረጉ ጥረቶች ተጨባጭ የሆነ ለውጥ ማምጣት ይኖርባቸዋል ሲሉ አሳስበዋል።

ሙስናን ለመከላከል ግልፀኝነትን ማስፈን፣ አሠራርን ማዘመን እንዲሁም ከአስተሳሰብ ጀምሮ ሪፎርም ማድረግ ሙስናን ለመከላከል ዋነኛ መንገዶች ናቸው ሲሉ ጠቁመዋል።

የሃይማኖት ተቋማት፣ ሲቪክ ማህበራት፣ ትምህርት ቤቶች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የግብረ-ገብነት እና የሞራል አስተምህሮዎችን ለተተኪው ትውልድ እና ለማህበረሰቡ የማስገንዘብ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ እንደሚገባም ከንቲባ አዳነች አስገንዝበዋል።

ማህበረሰቡ ሙስናን በማጋለጥ፣ በመጠቆም፣ እምቢ በማለት እና በቁርጠኝነት በመታገል ለሙስና ተግባራት ተባባሪ ባለመሆን ሀገራዊ ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

የመድረኩ ተሳታፊዎች በበኩላቸው፤ አሁን ላይ ሙስናን ለመዋጋት በየትምህርት ቤቶች የሚሰጠው የግብረገብ ትምህርት ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል ብለዋል።

በተቋማትም ብልሹ አሠራርን ለማስቀረት የዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች መዘርጋት ዋነኛ ሥራ ሊሆን ይገባል ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

# አገልግሎቱ  በአራት ወራት ከ920 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ ሰበሰበ

## - 462 ሀሰተኛ ሰነዶችም ጥቅም ላይ እንዳይውሉ አድርጓል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት ዓመት ባለፉት አራት ወራት 920 ሚሊዮን 606 ሺህ 523 ብር ገቢ መሰብሰቡን የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት አስታወቀ። 462 ሀሰተኛ ሰነዶች ጥቅም ላይ እንዳይውሉ በማድረግ በሀገር ላይ ሊከሰት ይችል የነበረን ጉዳት ማስቀረቱንም ገልጿል።

የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙዩኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚ አቶ አለምእሸት መሸሻ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አገልግሎቱ በተያዘው በጀት ዓመት የመጀመሪያ አራት ወራት 333 ሺህ 613 ጉዳዮችን አስተናግዷል። በዚህም 920 ሚሊዮን 606 ሺህ 523 ብር ገቢ አግኝቷል ብለዋል።

በአራት ወራት ለአገልግሎት ከቀረቡ ሰነዶች መካከል 462 ሀሰተኛ ሰነዶች መገኘታቸውን የጠቀሱት አቶ አለምእሸት፤ ከቀረቡት ሀሰተኛ ሰነዶች መካከል የማንነት ማረጋገጫ፣ የጋብቻ ማስረጃና ልዩ ልዩ የውክልና ሰነዶች መሆናቸውን ጠቅሰዋል። የሰነዶች ዲጂታላይዝ አለመሆን አገልግሎቱ የሰነዶችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የሚያደርገውን ጥረት አዳጋች አድርጎታል።

ሀሰተኛ ሰነዶች ጥቅም ላይ እንዳይውሉ ከማድረግ ባለፈ መሰል ችግሮችን ለመከላከልና ተጠያቂነትን ለማስፈን ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅርበት እየተሠራ መሆኑንም ጨምረው ገልጸዋል።

የአገልግሎት አሰጣጡን ለማዘመንና በቴክኖሎጂ የታገዘ ለማድረግ እየተሠራ ነው ያሉት ሥራ አስፈጻሚው፤ ሁሉንም የአገልግሎት ክፍያዎች በቴሌ ብር፣ በሲቢኢ ብርና  በሞባይል ባንኪንግ መክፈል እንዲቻል ተደርጓል። ይህም ደንበኞች የተቀላጠፈ አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ በኩል ጉልህ ሚና አበርክቷል ነው ያሉት።

አካል ጉዳተኞችና ሌሎች አቅመ ደካማ ደንበኞችን እንግልት ለማስቀረት የአገልግሎቱ ባለሙያዎች ደንበኞች ባሉበት ሄደው አገልግሎቱን እንዲሰጡ እየተደረገ መሆኑን አንስተው፤ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ከ3 ሺህ 600 በላይ ለሚሆኑ ደንበኞች ባሉበት አገልግሎት ተሰጥቷል ብለዋል።

የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት እየሰጣቸው ካሉ ነባር አገልግሎቶች በተጨማሪ የብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ ምዝገባ እያከናወኑ መሆኑን አመልክተው፤ በተያዘው በጀት ዓመት ከአንድ ነጥብ 5 ሚሊዮን በላይ ደንበኞች በአገልግሎቱ በኩል የብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ እንዲያገኙ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

አገልግሎቱ ለደንበኞች ዘመኑን የሚመጥን ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ነው ያሉት ሥራ አስፈጻሚው፤ ተገልጋዮች በመንደር የሚደረጉ ውሎች በአብዛኛው ለተለያዩ ችግሮች የሚዳርጉ መሆናቸውን በመገንዘብ ወደ ተቋሙ በመምጣት ተገቢውን አገልግሎት ማግኘት እንደሚችሉ ጠቁመዋል።

# የባሌ ተራሮች የቱሪዝም ሀብት ለዘላቂ ልማት እንዲውል ሰፊ ድጋፍ ያስፈልጋል

ገመቹ ከድር

ሮቤ፡- ሀገሪቱ ያላትን ቱሪዝም ሀብት በተለይም የባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ ተጠበቆ ለዘላቂ ልማት እንዲውል ሰፊ ድጋፍ እንደሚያስፈልግ ተገለጸ። የባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ ለዓለም ቅርስነት እንዲመዘገብ አስተዋጽኦ ላበረከቱ አካላት በባሌ ዞን ሮቤ ከተማ ትናንት ዕውቅና ተሰጠ።

በዕውቅና መርሃ-ግብሩ የተገኙ የት የቱሪዝም ሚኒስትር አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ እንደገለጹት፤ የባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ በአካባቢው ማህበረሰብ፣ ክልልና ፌዴራል መንግሥት መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት ጥረት የዓለም ቅርስ ሆኖ በዩኔስኮ ማስመዝገብ ተችሏል።

ፓርኩን በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሳይንስ፣ የትምህርትና ባህል ማዕከል (ዩኔስኮ) ማስመዝገብ ብቻውን በቂ አይደለም፤ የቱሪዝም ሀብቱ ተጠብቆ ወደ ዘላቂ ልማት ለመቀየር ሃላፊነት ወስዶ ሁሉም የበኩሉን ድርሻ መወጣት አለበት ብለዋል።

ኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ጥበቃ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ ኩመራ ዋቅጅራ በበኩላቸው፤ የአካባቢው ማህበረሰብ ያልተቋረጠ ድጋፍ በማድረጉ ባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ በቅርስነት መመዝገብ ችሏል።

የተፈጥሮ ሀብቱን በመንከባከብ ወደ ዘላቂ ልማት መቀየር የሁሉም አካላት ድጋፍ ይፈልጋል ያሉት አቶ ኩመራ፤ ፓርኩን በመንከባከብ ወደ ዘላቂ ልማት በመቀየር ወደ ትውልድ ለማሸጋገር ከሁሉም ይጠበቃል ሲሉ አመላክተዋል።

የሮቤ ከተማ ከንቲባ አቶ ንጋቱ ሞቱማ በበኩላቸው፤ ባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ በ1923 ዓ.ም የተቋቋመ ቢሆንም በተለያዩ ምክንያቶች ለዘመናት በዩኒስኮ ቅርስነት መመዝገብ እንዳልቻለ አስታውሰዋል።

አሁን ላይ በአካባቢው ህብረተሰብና በመንግሥት ጥረት በዓለም ቅርስ መዝገብ ውስጥ ማስመዝገብ ተችሏል። ስኬቱ ዞኑ የቱሪስት ማዕከል ከማድረጉም ባሻገር ለኤክስፖርት ግብዓት የሚሆኑ ግብርና ምርቶች የማምረት አቅሟ እንዲያድግ አድርጓል ብለዋል።

መንግሥት ፓርኩን ይጠልጥ ስኬታማ ለማድረግ መሠረተ ልማት ግንባታ ሥራዎችን ጨምሮ አምስት



ፎቶ፡- ሀዱሽ አብርሃ

በዕለቱ የተዘጋጀው የቱሪዝምና ባህላዊ ኤግዚቢሽን ተጎብኝቷል

ቢሊዮን ብር በላይ በጀት መድቦ እየሠራበት መሆኑን ገለጸው፤ ዞኑ ለፓርኩ በሚሰጠው ትኩረት አካባቢው የልማት ማዕከል መሆኑን አመላካች ነው ሲሉ ተናግረዋል።

የባሌ ዞን አስተዳዳሪ አቶ አብዱላኪም አሊይ፤ ባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ ከበርካታ ዓመታት በኋላ በዩኔስኮ ቅርስነት በመመዝገቡ አካባቢው ማህበረሰብ እንዲሁም የተለያዩ አካባቢ ዜጎችን ማስደሰቱን ገልጸዋል።

ፓርኩ የአካባቢውን ተፈጥሯዊ ሚዛን በመጠበቅም ትልቅ ዕገዛ እንዳለው ጠቁመው፤ ፓርኩ በሕብረተሰቡና በመንግሥት እስከ አሁን በተደረገው ጥረት ለ30 ሚሊዮን ዜጎች የሚበቃ የከባቢ አየር በጎ አስተዋጽኦ እያደረገ መሆኑን አመላክተዋል።

ፓርኩ የ80 አጥቢ እንስሳት፣ 310 የተለያዩ አዕዋፋት፣ ከአንድ ሺህ 600 በላይ የተለያዩ ዕጽዋቶችና የ40 ወንዞች መገኛ መሆኑን ገልጸው፤ ሁሉም አካላት ፓርኩን ለመንከባከብ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ጥሪ አቅርበዋል።

ከዕውቅና አሰጣጥ መርሀ-ግብሩ በተጓዳኝ የኢትዮጵያ ዱር እንስሳት ባለሥልጣን ከቱሪዝም ሚኒስቴር እና ከኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጋር በመተባበር የቱሪዝም ኤግዚቢሽን፣ ባሕላዊ ትርዒትና ጉብኝት አካሂደዋል።

ፓርኩን ከእሳት ቃጠሎ አደጋ ለማዳን ሕይወቱን አሳልፎ ለሰጠው ለአቶ ቢንያም አድማሱ የዕድሜ ልክ ዕውቅና ተሰጥቷል።

## ያልተጠቀምንበት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አካላት ትብብር ይሻል?

በአምራች ኢንዱስትሪ ምርምርና ልማት ማዕከል ተወካይ ሥራ አስኪያጅ አቶ መሀመድ ከድር፣ በኮሮና ወረርሽኝ፣ በሀገራችን በተለያዩ አካባቢዎች በነበሩ ጦርነቶች፣ በከተሞች መስፋፋት፣ በፋይናንስ አቅም፣ በውጭ ምንዛሪና በሌሎችም ምክንያቶች ባለፉት ዓመታት በቆዳ ኢንዱስትሪ ላይ የተሠማሩ ነጋዴዎችና ፋብሪካዎች ቁጥር መቀነሱ ከዘርፉ ይገኝ ለነበረው ገቢ መቀነስ ቀዳሚው ምክንያት እንደሆነ ይናገራሉ። ዘርፉን ለማነቃቃትና ወደ ቀድሞ ቦታው ለመመለስ ጅምር ተግባራት መኖራቸውንም ይጠቁማሉ።

ከእነዚህ ተግባራት መካከል አንዱ ምርት ያቆሙ ፋብሪካዎችን በመደገፍ ወደ ምርት እንዲገቡ ማድረግ መሆኑን የሚገልጹት ሥራ አስኪያጁ፤ ፋብሪካዎቹ ወደ ሥራ መመለስ ቢችሉ በየቦታው የሚጣለው ቆዳ እንዲሰበሰብና ወደ ምርት እንዲገባ፣ የምርት መጠንም እንዲጨምር በማድረግ ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ያላቸውን ተስፋ ይገልጻሉ።

ዘርፉ የሀገር ውስጥ የገበያ ፍላጎትን እንዳልተጠቀመ የሚናገሩት ሥራ አስኪያጁ፣ ፋብሪካዎቹን ወደ ሥራ እንዲመለሱ ከማድረግ በተጨማሪ የሀገር ውስጥ ገበያን በበቂ መጠን በመጠቀም ዘርፉን ለማነቃቃት መታሰቡንም ጠቁመዋል።

እርሳቸው እንዳሉት፣ በሀገር ውስጥ ገበያ ከፍተኛ የሆነ የወታደር ጫማ ፍላጎት አለ፤ ይህን መነሻ በማድረግም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በሚፈለገው ጥራትና መጠን ተፈላጊውን ጫማ ለማቅረብ እየተሠራ ይገኛል።

ከወታደር ጫማ በተጨማሪ የተጨማሪ ጫማ ለማምረትም ሙከራዎች እየተደረጉ መሆናቸውን የጠቆሙት ሥራ አስኪያጁ ተማሪዎች የሀገራቸውን ምርት እንዲጠቀሙ አመለካከት ላይ መሥራት እንደሚያሻም ያሳስባሉ። ከኢንዱስትሪው የሚገኘውን ገቢ ለማሻሻል በዘርፉ የሚታዩ ከገበያ፣ ከቆዳ ጥራትና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ላይ የነበሩ ችግሮችን እንዴት መቅረፍና ዘርፉን ማሻሻል ይገባል በሚሉት ላይ ከግብርና ሚኒስቴር፣ ከንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር፣ ከጥሬ ቆዳና ሌጦ አቅራቢዎች ማኅበር ጋር በጋራ የመሥራት ጅምሮች መኖራቸውንም ሥራ አስኪያጁ ጠቁመዋል።

በአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የቆዳ ቴክኖሎጂ ዘርፍ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ሚሻሞ ዋካሶ በበኩላቸው፣ ልክ እንደ አቶ መሐመድ ሁሉ የአምራች ኢንዱስትሪዎች በተለያዩ ምክንያቶች ከዘርፉ መውጣት ኢንዱስትሪው እንዲቀዛቀዝ እንዳደረገው ይናገራሉ። እነዚህን ኢንዱስትሪዎች ወደ ሥራ እንዲመለሱ በማድረግ ረገድ ማዕከሉ የሃሳብና የቴክኒክ ድጋፍ እየሰጠ እንደሚገኝም ይገልጻሉ። ወደ ሥራ ለመመለስ የመወሰኑ ጉዳይ የባለሀብቱን ቁርጠኝነትና ውሳኔ የሚፈልግ ነው ያሉት ሥራ አስፈጻሚው፣ ማዕከሉ ግን ባለው አቅም ሁሉ ፋብሪካዎች ወደ ቀድሞ የቆዳ ምርት ሥራቸው እንዲመለሱ የሚያደርገውን ጥረት አጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

እንደ ሥራ አስኪያጁ ማብራሪያ፣ ሥራ ያቆሙ ኢንዱስትሪዎች ወደ ሥራ ቢገቡ በሀገር ውስጥ ያለውንና ያለጥቅም እየተጣለ ያለውን የቆዳ ሀብት ለመሰብሰብ ትልቅ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ ይሆናሉ። እነዚህ ትልልቅ ፋብሪካዎች ለበርካቶች የሥራ እድል ፈጥረው የነበረ ሲሆን፣ ወደ ሥራ በሚገቡበት ወቅት ፋብሪካዎቹ በመዘጋታቸው ምክንያት ሥራ ላቆሙ ሠራተኞች የሥራ እድል ከመፍጠር አኳያ የሚኖራቸው አስተዋጽኦም ቀላል አይሆንም።

ወደ ውጪ የሚላከውን የቆዳ ኤክስፖርት መጠን በመጨመርም ዘርፉን ያነቃቃሉ የሚል ተስፋም ተጥሎባቸዋል። በተጨማሪም ወደ ዘርፉ ለመግባት ፍላጎት ያላቸውን ኢንቬስተሮችን በማበረታታት ረገድም ትልቅ አስተዋጽኦም ይኖራቸዋል ሲሉም አቶ መሀመድ ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ጥሬ ቆዳ አቅራቢዎች ማኅበር ፕሬዚዳንት አቶ ብርሃኑ አባተ፣ ማኅበሩ ረጅም ዓመታት እንዳስቆጠረ አስታውሰው፣ 80 ከመቶ በላይ የሆነው የቆዳ አቅራቢ በደረሰበት ኪሳራ ሳቢያ ከዘርፉ እየወጣና ዘርፉን እየቀየረ መሆኑን ይናገራሉ።

የኪሳራው መንስዔ በዋናነት ጥሬ ቆዳ የሚቀበሉ ፋብሪካዎች በሙሉ አቅማቸው እየሠሩ አለመሆናቸው እንደሆነም የጠቀሱት ፕሬዚዳንቱ፣ ዘርፉ በርካታ የሰው የሚይዝ ቢሆንም አሁን ያለበት ደረጃ ግን ሀገራችን በዘርፉ ካላት አቅም ጋር የሚመጣጠን እንዳልሆነ ይናገራሉ። በሀገራችን ያለው ወደ ምርት መቀየር የሚችል የቆዳ ሀብትም በየአካባቢው እየተጣለ እንደሚገኝም በቁጭት ይናገራሉ።

ማኅበሩ በዘርፉ ያሉ ችግሮችን ለመፍታት ከሌሎች የመንግሥት አካላት ጋር የቆዳ አቅራቢ ነጋዴውን ወክሎ እየሠራ እንደሆነ በማንሳት፣ ዘርፉን የማንሳት ትልቅ ኃይል ያለው ከምንግሥት ዘንድ ነው ይላሉ። በቅርቡ የተጀመሩ መልካም ጅማሮዎች መኖራቸውንም በማንሳት መንግሥት ለዘርፉ ትኩረት ሰጥቶ ለዓለም ገበያ የሚመጥን ምርት እንዲኖር ነጋዴዎችን፣ ቄራዎችንና የሚመለከታቸውን አካላት አስተባብሮ መሥራቱን አጠናክሮ ቢቀጥልና በጀመረው ልክ መጓዝ ከቻለ ውጤት ያመጣል የሚል ተስፋ እንዳላቸውም ተናግረዋል። ማኅበሩም ከዘርፉ የወጡ ነጋዴዎችን በመመለስና በሌሎችም ጉዳዮች ዘርፉ ላይ የሚሠሩ አካላትን በሚችለው አቅም ለመደገፍ ዝግጁ መሆኑንም አስታውቀዋል።

## “ኢትዮጵያውያን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እንዲጎለብቱ ስለሚያግዝ ኢትዮጵያውያን በመተባበር ለሀገራቸው ሰላም ዘብ ሊቆሙ ይገባል ብለዋል።

የሙስሊሙ ማህበረሰብ ሰላማዊ ትግል የመከባበርና የመግባባት ስሜትን በመፍጠር ረገድ ተምሳሌት ይሆናል ያሉት ሼህ ሐጂ ኢብራሂም፤ ሁሉም ዜጋ በመተባበር የሀገሩን ሰላም ለማስጠበቅ የድርሻውን ሊወጣ እንደሚገባ ጥሪ አቅርበዋል።

ኢትዮጵያ አሁን ያለችበትን የፀጥታ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ችግሮችን በንግግርና በውይይት በመፍታት ውስጣዊ ሰላምን ማረጋገጥ እንደሚገባ ተናግረዋል።

በተለያዩ አካባቢዎች ያሉ ግጭቶች በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱና ሰላም እንዲመጣ መመካከርና በበቂ ሁኔታ መነጋገር አስፈላጊ መሆኑን ሼህ ሐጂ ኢብራሂም ገልጸዋል።

የአዲስ አበባ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት ፕሬዚደንት ሼህ ሱልጣን አማን ኤባ በበኩላቸው፤ ከለውጡ በኋላ መንግሥት የእስልምና ጠቅላይ ምክር ቤት ሕጋዊ ሰውነት እንዲያገኝ የሚያስችል አዋጅ ማጽደቁን ጠቁመው፤ የሸሪዓ መርህን የተከተለ የፋይናንስ ተቋም እንዲቋቋምና ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በገቡት ቃል መሠረት የሙስሊሙ ማህበረሰብ የተለያዩ ጥያቄዎች ምላሽ ማግኘታቸው የሚያስመሰግን መሆኑን አመላክተዋል።

ኢስላማዊ እሴቶችን ያከበረ የፋይናንስ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጡ ተቋማትን ወደሥራ የማስገባቱ ጥያቄ በመመለሱ መንግሥት ለማህበረሰቡ የሰጠውን ትኩረት ያሳያል ሲሉ ገልጸዋል።

ከእምነቱ ጋር የተያያዙና ምላሽ ለማግኘት በሂደት ላይ ያሉ የተለያዩ ጥያቄዎች መኖራቸውን ጠቁመው፤ ጥያቄዎቹ ምላሽ እንዲያገኙ ከከተማ አስተዳደሩ ጋር በመተባበር እየሠራን ይገኛል ብለዋል፡፡

መንግሥት የሕዝበ ሙስሊሙን የረጅም ጊዜ የተቋም ጥያቄዎች ምላሽ እየሰጠ በመሆኑ ምስጋና እንደሚገባው ተናግረዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ፤ የእምነት ተቋማት ለኢትዮጵያ ሰላም ያበረከቱት አስተዋፅኦ ከፍተኛ በመሆኑ ሊመሰገኑ እንደሚገባም ገልፀዋል፡፡

መንግሥት በሕጋዊ መንገድ የሚነሱ ጥያቄዎችን ለመፍታት ምን ጊዜም በሩ ክፍት መሆኑን የጠቆሙት ከንቲባዋ፤ ስለሀገር ሰላም ሲባል የሚከናወኑ በጎ ጥረቶች ተጠናክረው ሊቀጥሉ እንደሚገባ አመላክተዋል።

የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ለጠቅላይ ሚኒስትረ ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እና ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ያበረከተውን የምስጋና ሽልማት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ተቀብለዋል።

በመድረኩ የመንግሥት ከፍተኛ የሥራ ሃላፊዎች ፣ የተለያዩ ሀገራት አምባሳደሮችና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል።

## “ኢትዮጵያ በአፍሪካ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ክሬምሊን ቤተ መንግሥት አሌክዛንደር አዳራሽ ተቀብለዋል።

በሥነ-ሥርዓቱ ላይ በሩሲያ ፌዴሬሽን የኢትዮጵያ ልዩ መልዕክተኛና ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር ቻም ኡጋላ ኡሪያት የሹመት ደብዳቤያቸውን ለሩሲያው ፕሬዚዳንት አቅርበዋል።

አምባሳደሩ የሹመት ደብዳቤያቸውን ባቀረቡበት ወቅት ፕሬዚዳንት ፑቲን ባስተላለፉት መልዕክት፤ ኢትዮጵያና ሩሲያ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ከመሠረቱ 125 ዓመታትን ያስቆጠሩ ወዳጅ ሀገራት መሆናቸውን አንስተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በቅርቡ በሩሲያ ይፋዊ የሥራ ጉብኝት በማድረግ የተለያዩ የትብብር ስምምነቶች መፈረማቸው ግንኙነቱን ከፍ ወዳለ ደረጃ እንዳሻገረው ፕሬዚዳንቱ አስታውሰዋል።

በጉብኝቱ ወቅት በትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ፣ በቴሌኮሙኒኬሽን እንዲሁም በሌሎች ዘርፎች የተለያዩ ስምምነቶች መደረጋቸውን የጠቀሱት ፕሬዚዳንቱ፤ ስምምነቶቹ ሲተገበሩ የሩሲያና የኢትዮጵያን ትብብር ወደ ላቀ ደረጃ እንደሚያሸጋግሩት ገልፀዋል።

ኢትዮጵያ ብሪክስን ለመቀላቀል ያቀረበችውን ጥያቄ ሩሲያ ስትደግፍ እንደነበር ገልጸው፤ አሁን ላይ ኢትዮጵያ ብሪክስን መቀላቀሏ የሁለቱን ሀገራት ግንኙነት የበለጠ እንደሚያጠናክረውም መናገራቸውን በኢትዮጵያ የሩሲያ ኤምባሲ መረጃ አመልክቷል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## በታዳሽ ኃይል አማራጮች ላይ ያተኮረው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ግንባታ!

ዓለማችን በአየር ንብረት ለውጥ መታመስ ከጀመረች ውላ አድራለች። ጎርፍ፣ ድርቅ፣ ሰደድ እሳት፣ ከባድ አውሎ ነፋስና ሱናሜን የመሳሰሉ ክስተቶች ዕለት ከዕለት እየፈተኗት፤ የሰዎችን ኑሮም እያመሳቀሉ ቀን ከሌት እረፍት ነስተዋታል። እነዚህ ክስተቶች ደግሞ የሰው ልጆች የሥራ ውጤት እንደመሆናቸው የሰው ልጆችን የመፍትሔ አካልነት አብዝተው የሚሹ ናቸው።

በዚህ ረገድ ቀድመው ያደጉ እና ከባድ ኢንዱስትሪዎችን ተግብረው የኢኮኖሚያቸው ማዕከል ያደረጉ ሀገራት ቀዳሚውን ድርሻ ይይዛሉ። ምክንያቱም ባለ ግዙፍ የኢንዱስትሪ ሀገራት፤ ከኢንዱስትሪዎቻቸው በሚወጡ በካይ ጋዞች አማካኝነት በከባቢ አየር ላይ የሚፈጥሩት ጫና ለአየር ንብረት ለውጥ ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛል።

የችግሩ ምንጮች እንዲህ አይነት ባለ ግዙፍ ኢንዱስትሪ ባለቤት የሆኑ ሀገራት ይሁኑ እንጂ፤ ችግሩ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ሰለባዎች ግን ለአየር ንብረት ለውጥ ችግር እዚህ ግባ የሚባል አበርክቶ የሌላቸው ድሃ ሀገራትም ጭምር ናቸው። ዛሬ ላይ በአፍሪካም፣ በአውሮፓም፣ በአሜሪካም ሆነ በሁሉም የዓለም አካባቢ ያለልዩነት የሚታየው ጭንቅና መከራም ለዚህ ጉዳይ ሁነኛ ማሳያ ነው።

ምንም እንኳን የችግሩ መከሰት ቀዳሚ ተብለው የሚጠቀሱ ሀገራት ቢኖሩም፤ እነዚህ ሀገራት ከችግሩ ለመውጣት በሚደረገው ጥረት ውስጥ ግን የቀዳሚነታቸውን ያህል ቀድመው መገኘት አልቻሉም። ለምሳሌ፣ ዛሬ ላይ አንዳንድ የአደጉ ሀገራት በተደጋጋሚ በሱናሚ ቢመቱም፣ ለሱናሚው መከሰት ምክንያት መሆናቸውን አውቀው ለችግሩ መቃለል እያደረጉ ያሉት የመፍትሔ ጥረት እዚህ ግባ የሚባል አይደለም።

እነዚህ ሀገራት ምናልባት ችግሩን ለመሻገር የሚያስችላቸው የኢኮኖሚም፣ የቴክኖሎጂም አቅም ገንብተው ሊሆን ይችላል። ሆኖም ይሄን ማድረግ የማይችሉ ሀገራት ግን ዜጎቻቸው ለተደጋጋሚ ችግር ሲጋለጡ፤ ሀገራቱም በብርቱ ሲፈተኑ ማየት የተለመደ ሆኗል።

ኢትዮጵያም የዚህ አንዷ ሰለባ ናት። ምንም እንኳን ኢትዮጵያ ለአየር ንብረት ለውጥ ችግር መከሰት ያላት አበርክቶ እዚህ ግባ የሚባል ባይሆንም፤ ችግሩ ባስከተለው የድርቅ፣ ጎርፍና መሰል አደጋዎች ግን ከዓመት ዓመት ዋጋ እየከፈለች፤ ዜጎቿም ለከፋ ችግርና እንግልት እየተዳረጉባት ያለች ሀገር ናት።

በመሆኑም እንደ ሀገር ከዚህ ችግር ለመውጣት ብቻ ሳይሆን፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ የራስን አበርክቶ ለማድረግ ሲባል ኢትዮጵያ የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማት ላይ አተኩራ እየሠራች ትገኛለች። በዚህም ችግኝ ከመትከል ጀምሮ፣ በግብርናው ዘርፍ ውጤታማ ለመሆን የሚያስችሉ የተፋሰስ ልማት ሥራዎችን በስፋት ተግብራ ውጤት አምጥታለች።

ከዚህ በተጓዳኝ በከባቢ ላይ ጉዳት ከሚያደርሱ ኃይል የማምረትና አጠቃቀም ተግባራት ተቆጥባ፤ በታዳሽ ኃይል ምርትና አጠቃቀም ላይ ትኩረቷን አደረገች። በዚህም በርካታ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ግድቦችን ገነባች፤ የንፋስ ኃይል ማመንጫዎችን ተከለች፤ የፀሐይ ኃይል ማምረቻዎችን አስፋፋች፤ የእንፋሎት ኃይል ማመንጫንም እንደ አማራጭ መተግበር ጀመረች።

መለስተኛ ከሆኑ ግድቦች ጀምራ እስከ ግዙፉ የዓባይ ግድብ ድረስ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫዎችን እውን አደረገች፤ በቀጣይም በርካታ ፕሮጀክቶችን ለመተግበር ትልም አስቀመጠች። በአዳማ እና አሸጎዳ የተጀመሩ የንፋስ ኃይል ማመንጫዎችና አሁን ላይ 300 ሜጋ ዋት የማመንጨት አቅም ያለውን ግዙፍ የንፋስ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት በሶማሌ ክልል ለመትከል የሚያስችል ጉዞን አደረገች።

ታዳሽ ኃይልን የማምረት ብቻ ሳይሆን የመጠቀም ልምዷንም አዳበረች። በቤተሰብ፣ በተቋማትና በድርጅቶች ብሎም በፋብሪካዎች ጭምር ታዳሽ ኃይሎች ቀዳሚ የኃይል አማራጭ እንዲሆኑ ተደረገ። ከፍ ያለ የአየር ብክለት የማድረስ አቅም እንዳላቸው የሚነገርላቸው ተሽከርካሪዎች ጭምር በታዳሽ ኃይል ላይ የተመሠረተ አጠቃቀም እንዲኖራቸው በሕግ ታግዛ ወደ ተግባር ገባች።

በካይ ጋዝን ወደ ከባቢ የመልቀቅ ሂደትን የመቀነስ ብቻም ሳይሆን፤ ሌሎች በሚለቁት በካይ ጋዝ ዓለማችን የሚደርስባትን አደጋ ለመቀነስ በአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብሯ ለዓለም ሳንባን የመፍጠር እንቅስቃሴ ውስጥ ገባች። ይሄ ደግሞ ዘርፈ ብዙ ፋይዳ ያለው ነው።

ተግባሩ በአንድ በኩል የተመናመነውን ሀገራዊ የደን ሽፋን የመመለስ፤ በሌላ በኩል በምግብ ራስን የመቻልና የሥራ ዕድል የመፍጠር፤ ከዚህ አለፍ ሲልም በ50 ቢሊዮን ችግኞች አጋዥነት የዓለምን የአየር ንብረት ለውጥ ሚዛን ማስጠበቅን የመሳሰሉ ከፍ ያሉ አበርክቶዎች ያሉት ነው።

በዚህ መልኩ የሚከናወነው የኢትዮጵያ የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ ሂደት፤ እንደ ሀገር ልማትን፣ እንደ ዓለምም እፎይታን የሚያስገኝ ከፍ ያለ ተግባር መሆኑ እሙን ነው። ይሄ ደግሞ ዛሬ ላይ ዓለማችን በገጠማት ችግር ምክንያት እንደ ሀገርም ከምንቸገርበት የአየር ንብረት ለውጥ መዘዝ የሚታደግ እንደመሆኑ፤ ተግባሩ ሊወደስም፣ ሊታገዝም የሚገባው ነው። በተለይም ለአየር ንብረት ለውጡ ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው የበለጸጉ ሀገራት የኢትዮጵያን መፍትሔ አምጪ መንገድ በሁሉም መልኩ ሊያግዙ ይገባል። ምክንያቱ ደግሞ በታዳሽ ኃይል ላይ የተመሠረተው የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ግንባታ ጉዞ፤ ከራስም በላይ ለዓለም ፈውስን ይዞ የቀረበ ነውና!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ከኑሮ ውድነት ባሻገር

ሙሉጌታ ብርሃኑ

ኑሮ ተወደደ..ኑሮ ተሰቀለ የሁላችንም የዕለት ተዕለት ሰሚ ያጣ ጩኸታችን እንደሆነ ውሎ አድሮ ከቆመጠጠ ሰነባበተ። ኑሮ ተወደደ ተሰቀለ እያልን እዬዬ..ብንልም፤ዳሩ ግን የተሰቀልነው እኛ እንጂ እሱ አይደለም። ኑሮ መወደዱን እንዲያቆም እንመኛለን...ኑሮ ግን መቼም ቢሆን መወደዱን አያቆምም።

ሁላችንም እራሳችንን ከደሙ ንጹሕ እያደረግን የምናዋድደው እኛው ነንና እሱም መወደድን አይጠላም። መሣሪያ ይዞ እንደወረረን ጠላትም በክተት አዋጅ፤ በሽምቅ ውጊያም የምናሸንፈው አይደለም። መለስ ብለን እንደ ግለሰብ እያንዳንዳችን ኃላፊነታችንን እስካልተወጣን ድረስ የኑሮ ውድነትን ማሸነፍ ዘበት ነው።

ኑሮ ለምን ተወደደ? ስንል ሁሌም ከአፋችንም ከአዕምሯችንም የማይጠፉ ከጥያቄው ቀድመው የሚመጡልን ምላሾች አሉ። ነገር ግን ከእነዚህ ባሻገር በኑሮ ውድነት ውስጥ ሳናጤናቸው እጅና እግራችንን ጠፍንገው ስላሰሩን አንዳንድ ጉዳዮች እናንሳ።

ኑሮ ለምን ተወደደ? አዎን የምናውቃቸው እልፍ መንስኤዎች አሉ። በአጭር መንገድ ለመከበር በሚደረግ ሩጫ ክብረወሰን ሰባሪው ብዙ ሆኗል። 'ማትረፍ' ሳይሆን 'መቦትረፍ' የብዙ ሰው ስንቅ እራት ሆኗል። ዛሬ የምናየው የኑሮ ውድነት በዚህን ያህል ደረጃ ከፍ ማለቱ የእውነትም ለዚህ የሚያበቃን ምክንያት ኖሮ ሳይሆን ለራሱ ለማደላደል አጋጣሚዎችን የሚጠባበቅ ሰበብ ፈላጊ በመብዛቱ ነው።

በርግጥ ሁላችንም ነጋዴዎች ሆነናል። በአንድም ሆነ በሌላ በኑሮ ውድነቱ ውስጥ እጃችን አለበት። አስተዋፅዖ የምናደርግባት አንዲት ቦታም አለች። እኛ ሁላችንም አንደኛው ቦታ ላይ ገዢ፤ አንደኛው ቦታ ላይ ደግሞ ሻጭ ነን። ሻጭ ስንል የግድ በንግዱ ዓለም የተሠማራ ማለት አይደለም።

የኑሮ ውድነት ማለትም የቁሳቁስ ብቻ እንዳልሆነ ልንገነዘብ ይገባል። ትላንት ሻጭ የነበረው ሰው ዛሬ ገዢ ሆኖ እኛ ጋር ሊመጣ ይችላል፤ ይህ በኑሮ ቀለበት ውስጥ ሁሌም ያለ ነው። የኑሮ መወደድ መንስኤም የሚገኘው በዚሁ ቀለበት ውስጥ ነው። ቲማቲም ጨመረ ብሎ የሽንኩርት ዋጋ የሚጨምር፤ ጤፉ ከየት እንዳመጣው ባናውቅም ዶላር ጨመረ ብሎ የጤፍ ዋጋ የሚጨምር ነጋዴ ብቻም ሳይሆን ቆርቆሮና ሚስማር ተወደደ ብሎ ባረጀ ባፈጀው ቤት ላይ ዋጋ የሚጨምር የቤት አከራይም ተፈጥሯል።

ከኑሮ መወደዱ ይልቅ የኛ ማዛመዱ በዛ። አንዲት ኑሮ ውድነት በኛ ሰበብ እየተባዛች ብዙ እጥፍ ትወልዳለች። ትልቁ ችግራችን እራስ ወዳድነት ነው። በአንዱ ያጣነውን በሌላ ለማካካስ ስንማስን ሙሉ ገበያው እሳት በእሳት ይሆናል። ከአንዲት ቦታ በተለኮሰች እሳት ወደ ሁሉም እየተሰራጨ የሰደድ እሳት ይሆናል።

አንዱ የጅምላ አከፋፋይ የጨመረውን ሂሳብ የለመዱትን ትርፍ ማጣት የማይፈልጉት ተረካቢዎችም፤ የተቀበሉትን ጭማሪ ወስደው ለገዢዎቻቸው በችርቻሮ ያከፋፍሉታል። የስኳርን የዋጋ ጭማሪ የሰማችው ያቺ ምስኪን የጨው ዕቃ እያልን የምናላግጥባት ጨው እንኳን፤ እኔስ ከማን አንሼ ስትል ትከተላለች።

እንግዲህ ማን ቀረ? በአንዲት የበርበሬ መወደድ ምክንያት በድስቱ ውስጥ የሚገኙ አባላት በሙሉ ተባብረው ወጥ ሳይሆን የእሳት እረመጥ ይሆናሉ። ከጤፉ የምትወለደው እንጀራም ምሕረት የላትም ትቀጥላለች። ይህን ከመሰለው የውስጥ ለውስጥ ፍትጊያዎቻችንን አለፍ ስንል፤ የኛ ኑሮ እሳት ለብሶ እሳት ጎርሶ እኛኑ እንዲውጠን ካደረጉን ነገሮች መካከል ሌላ ውጫዊ ተውሳክም አለብን።

> **የኛን ኑሮ በቁሙ እየገዘገዘው ኑሮ ውድነቱን ያከናነበን ሌላኛው ጉዳይ 'ሜድ ኢን ፈረንጅ' መሆናችን ነው። ሥልጣኔ ይሁን የስንፍና መቅኔ ከጉልበታችን ገብቶ ውጭ ውጭውን ማየት አብዝተናል**

የኛን ኑሮ በቁሙ እየገዘገዘው ኑሮ ውድነቱን ያከናነበን ሌላኛው ጉዳይ 'ሜድ ኢን ፈረንጅ' መሆናችን ነው። ሥልጣኔ ይሁን የስንፍና መቅኔ ከጉልበታችን ገብቶ ውጭ ውጪውን ማየት አብዝተናል። ከኛ እውቀት የፈረንጅ እውቀት፤ ከኛ ጥበብ የፈረንጅ ጥበብ፤ ከኛ የወይን ጠጅ የፈረንጅ ሀሞት፤ ከኛ ብዕር ይልቅም የፈረንጅ እርሳስ አድምቆ የሚጽፍ መስሎ ይሰማናል። ታዲያ እኛ የፈረንጅ የሆነ ነገር ሁሉ ሲያምረን ኑሮስ ለምን መወደድ አያምረውም?።

የባሕላችንን ብቻ ሳይሆን የአኗኗር ዘያችንንም አመሳቅለነዋል። የኛ የሆነውን ከማምረትና ከመጠቀም ይልቅ የእነርሱን ማከፋፈልና መሸቀጥ አብዝተናል። ገንዘብ ስላለን ብቻ ምንም ሳይመስለን እንደቀልድ የምናደርጋቸው ነገሮች፤ ከኛ አልፈው ማኅበረሰባችንንም መጠራረግ ጀምረዋል። በሀገር ውስጥ የሚመረቱትን ምርቶች እኛ ካልተጠቀምናቸው ማንስ ሊጠቀማቸው ነው?

ለመብላቱም...ለመልበሱም...ለመዋቡም ዓይናችን የሚያየው፤ ልባችንም የሚወደው ባሕር አቋርጦ የመጣውን የሩቅ ተጓዥ ነው። በወርቅ ከተለበጠው 'ሜድ ኢን ኢትዮጵያ' ይልቅ በነሐስ በተለበጠው 'ሜድ ኢን ፈረንጅ' ኩራት ይሰማናል። ጫማው ቬትንሃም፣ ካልሲውም የጆርዳን፣ ሱሪው ደግሞ ታይላንድ፣ ሹራቡ ከአሜሪካ፣ ቲሸርቱ ካናዳ፣ ኮፍያው ከጀርመን ካልሆነ በቀር ለብሶም የለበሰ የማይመስለው ስንት አለ...በአልባሳቱ ብቻም ሳይሆን በሌላውም። ዓይንና ልባችን በምንዛሪና በግዙፍ ታክስ በሚገቡት ላይ ከሆነ እንዴትስ ኑሮ አይወደድ?

"እኔ እንኳን የሀገር ውስጥ ምርት ብዙም አልጠቀምም..." በማለት የውጭ ምርትን መጠቀም እንደ ልዩ ክብር አድርገው ሲናገሩ የሚታዩና የሚሰሙ ጥቂት አይደሉም። ከፋቱ ያለው የውጭ ምርት መጠቀማችን ላይ አይደለም። ነጋዴውም ሆነ አምራቹ ሁሌም ትርፍን ይፈልጋሉ። የተጠቃሚው ፍላጎት የውጭ ምርቶች ላይ ከሆነ፤ ፍላጎቱን ተከትለው እነርሱም ፊታቸውን ወደ ውጭ ምርቶች ያዞራሉ።

የዛኔ መውጫ መግቢያውን ያጣው የሀገር ውስጥ ምርት ቀስ በቀስ ከገበያው ጨዋታ ውጭ ይሆናል። የሀገር ውስጥ አምራችና ምርትን መገፍተር ማለት በሌላኛው መልኩ የገዛ ገንዘባችንን ከኪሳችን እየገፈተርን ኑሮ በውድነት የምትበስልበትን እሳት ማቀጣጠል ማለት ነው።

የሀገርና የራስ ምርትን አናንቆ በካልቾ እየጠለዙ ኑሮ ውድነት እንዲቀንስ መሻት፤ የሲኦል በር ላይ ቆመው ገነትን እንደመመኘት ነው። የኑሮ ውድነት እንዲባባስ የሚያደርጉት ከውጭ የሚገቡ ምርቶች ብቻም ሳይሆኑ አላግባብ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባው የውጭ ሀገር ገንዘብም ሌላኛው የቀውሱ መንገድ ነው።

በሌላ መንገድ ሀገራችን የምትከተለው የነፃ ገበያ ሥርዓት መሆኑ ይታወቃል። ነገር ግን በነፃ ገበያ ጥላ ስር ተቀምጠው "ይሄ እኮ ነፃ ገበያ ነው...ካልተመቸህ መተው ትችላለህ" እያሉ፤ የሕዝብን ኪስ የሚያኝኩትን ነፃ ዘራፊዎችን መንግሥት አንድ ሊላቸው ይገባል። በነፃ መተሳሰብና ፍቅር የኖረን ሕዝብ በነፃ ገበያ ሲመነተፍ እያዩ ዝምታ አያሻም።

አሁን አሁን በእጅጉ አሳሳቢ እየሆነ የመጣው የደላሎች ነገር ደግሞ ሌላው አሳሳቢ ጉዳይ ነው። በገበያው መግቢያና መውጫ ቆመው ሁሉንም ያለ እኔ አይሆንም በማለት ገዢና ሻጭ፤ ፈላጊና ተፈላጊ በቀጥታ እንዳይገናኙ በማድረግ ውድነቱን አፋፍመውታል።

በቤት ኪራዩ ብንመለከት፤ ከአከራዩ ምስጋናና ተጨማሪ ጉርሻ ለማግኘት ሲል በእጅ እግር እየገባ ቀድሞ ከታሰበው በላይ እንዲከራይ የሚያደርግ ብዙ ነው። እንግዲህ ከዚያን ወዲህ ኑሮ ሽቅብ እንጂ እንደ ውሃ ቁልቁል አይፈስም፤ ይህን የሰማ ጎረቤትም ይቀጥላል።

ኑሮ ውድነት በየትኛውም ዓለም ውስጥ ያለና የሚኖር ቢሆንም ድህነታችን የባሰውን ገልጦ አሳይቶናል። ኑሯችን፤ ኑሮ ውድነት ምን እንደሆነ ሰምተው ከማያውቁት ጋርም ጭምር ነውና ከመተሳሰቡ ይልቅ መተዛዘብ አብዝተናል።

እንግዲህ ብለነዋል ፤ ማናችንም ሁሉም ቦታ ላይ ገዢ፤ ሁሉም ቦታ ላይ ሻጭ አይደለንም... ስለዚህ አንተም ተው እኔም ልተው ተባብለን በብልሃት መኖር ስንችል፤ ተያይዞ ማደግ ይመስል ተያይዞ በኑሮ ውድነት መዋደቅን ምን አመጣው?!።

# ትዳርን በመጠበቅ ትውልድን መታደግ

**ስሜነህ ደስታ**

ትዳር የሚለውን ቃል፣ በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል ባልና ሚስት የመሆን ፍቃደኝነት ላይ የሚመሠረትና ቤተሰብ የመገንባት ነፃ ፍላጎት ነው በሚል ፍቺ ልንሰጠው እንችላለን። ይህ ነፃ ፍላጎት በሁለቱ ጥንዶች መካከል የሚገኙ የቤተሰብ አባላትን በዝምድና የሚያስተሳስር፤ በማኅበረሰቡ መካከል ትስስር የሚፈጥር፤ ሕጋዊ፣ ማኅበራዊ እና ሃይማኖታዊ መስተጋብሮችን ያካተተ ነው።

እንደ አንድ ትልቅ ማኅበራዊ ተቋምም ትዳር የተከበረ እና የተቀደሰ፤ ከዚህ የተነሳም በየትኛውም ማኅበረሰብ ውስጥ ከፍተኛ ማኅበራዊ፣ ሃይማኖታዊ እና ሕጋዊ ጥበቃ የሚደረግለት ተቋም ነው። በኛም ሀገር የቀደሙት አባቶቻችንና እናቶቻችን የትዳርን ክቡርነት ተረድተው፤ ከፍ ያለ ጥበቃ ሲያደርጉለት ቆይታል።

ይህ ሀገራዊ እውነታ አሁን አሁን መልኩን እየቀየረ፤ የትዳር ጉዳይ ወቅታዊ አጀንዳ መሆን የሚችልበት ደረጃ ላይ እየደረሰ ስለመገኘቱ መረጃዎች ያመለክታሉ። ለዚህም በአዲስ አበባ ከተማ በ2015 ዓ.ም. በጀት ዓመት የተመዘገበው የፍቺ መጠን፣ ከ2014 ዓ.ም. ጋር ሲነጻጸር 60 በመቶ ብልጫ እንዳለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሲቪል ምዝገባና ነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ መግለጹ አንዱ ማሳያ ነው።

ይህ አኀዝ የኢትዮጵያ የቤተሰብ ሕግ የተከበረ ለሆነው ትዳር ተገቢ የሆነ ጥበቃ አያደርግም፤ በተለይ ፍቺ ለማድረግ ለሚፈልግ ባለትዳር ሕጉ በሩን ከፍቶ ነው የሚያስተናግደው የሚል መከራከሪያ ይዘው ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ለሚሞግቱ ዜጎች የመከራከሪያ አቅም እየሆናቸው ይገኛል።

በአንድ ወቅት ለንባብ የበቃ መረጃ እንደሚያመለክተው፣ የሕንድ አየር ኃይል አባል የሆኑት የ89 ዓመቱ ኒርማል ሲንግ ከ40 ዓመታት በፊት ከተለዩዋቸው ሚስታቸው ፓራምጂት ካውር ፓኔሳር ጋር በይፋ በፍርድ ቤት ለመፋታት ለ27 ዓመታት ያደረጉት ጥረት ሳይሳካ ቀርቷል። ጥንዶቹ የተጋቡት በፈረንጆቹ 1963 ሲሆን፣ በጋብቻቸውም ሦስት ልጆችን አፍርተዋል። ጋብቻው ከተፈጸመ ከ21 ዓመታት በኋላ ባል፣ ከሚስታቸው ጋር በሥራ ምክንያት በመራራቃቸው «ሚስቴ እና ልጆቼ ወደኔ ቀረብ ብላችሁ ኑሩ» በማለት ያቀረቡት ሀሳብ በሚስታቸው ውድቅ ተደረገባቸው።

በመምህርነት ተቀጥረው ሲሠሩ የነበሩት ሚስት «ሥራዬን ለቅቄ አልመጣም» ማለታቸው ልዩነቱን አስፍቶት ተለያዩ። ልዩነቱ በፍርድ ቤት የፀና እንዲሆንም ኒርማል በፈረንጆቹ 1996 ወደ ወረዳ ፍርድ ቤት አቤት ይላሉ። ይሁን እንጂ ባለቤታቸው ፓራምጂት ትዳራቸውን ለማጽናት የሚችሉትን ሁሉ ማድረጋቸውን በመጥቀስ በመከራከራቸው ፍርድ ቤቱ የፍቺ ጥያቄውን ውድቅ አደረገው።

ኒርማል ከሕንድ አየር ኃይል በጡረታ ከወጡ በኋላም ከ40 ዓመት በፊት ከተለዩዋቸው ሚስታቸው ጋር በፍቺ እንዲለያዩ ላለፉት 27 ዓመታት ፍርድ ቤት ተመላልሰዋል። የ89 ዓመቱ አዛውንት ከዚህ በፊት ያቀረቡት ተደጋጋሚ ጥያቄ ምላሽ ባያገኝም የ27 ዓመት ድካማቸው እንደሚያበቃ ተስፋ አድርገው ለሕንድ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍቺ ጥያቄያቸውን አቅርበው ነበር።

በ82 ዓመታቸው ፍርድ ቤት የቀረቡት ፓራምጂት ፍቺውን እንደሚቃወሙና የ89 ዓመት ባላቸውን(ቢለያዩም ፍቺው ስላልፀደቀ) ለመንከባከብ ዝግጁ መሆናቸውንና በዚህ እድሜያቸው ፍቺ እንደማይፈልጉ ተናግረዋል። ዳኞችም ትዳር የተቀደሰና የተከበረ ተቋም መሆኑን በመጥቀስ «ለፍቺ የሚያበቃ አሳማኝ ምክንያት አላገኘንም» በሚል የፍቺ ጥያቄውን ባለመቀበል ውድቅ አድርገውታል።

> **ትዳር ሲመሠረት፣ ቤተሰብ ለማስተዳደር የሚያስችል የንቃተ-ሕሊና ማዳበሪያ ኮርስ በማዘጋጀት ኮርሱን ወስዶ ማጠናቀቅ ለሁለቱም ተጋቢዎች ግዴታ ቢሆን እላለሁ**

በሕንድ ሀገር ፍቺ እንደጋብቻ ቀላል አይደለም። በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍል ፍቺ እንደነውር ስለሚታይ ሕጉም ለትዳር ከፍተኛ ጥበቃ ያደርጋል። ባል ወይም ሚስት ፍቺ ቢፈልጉ እንኳን አሳማኝ የበደል ወይም የጥፋት ማስረጃ ማቅረብ ስለሚኖርባቸው በፍርድ ቤት ጥያቄያቸው እምብዛም ተቀባይነት አይኖረውም። ጥናቶች እንደሚያሳዩት በሕንድ ከ100 የትዳር ፍቺ ጥያቄ በፍቺ የሚጠናቀቀው አንዱ ብቻ ነው።

ቀደም ሲል ለማንሳት እንደሞከርኩት በመዲናችን አዲስ አበባ፤ በዓመት 60 በመቶ ጭማሪ ያሳየ የፍቺ ምዝገባ እንደተካሄደ ይገኛል። እነዚህ ብቻ ሳይሆኑ በወደድኩህ ወደድኩሽ ትዳር ተመሥርቶ፤ "በደበረኝ" ሰበብ እንደው እንደዋዛ ለአቅመ ምዝገባ ሳይበቁ የተደረጉ ፍቺዎች ደግሞ በየቤቱ መኖራቸው እሙን ነው።

ለጊዜው በየቤቱ የሚከናወኑትን ፍችዎች ትተን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሲቪል ምዝገባና ነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ ቀርበው ትዳራቸውን በፍቺ ያጠናቀቁትን ብቻ የአንድ ዓመት ልዩነቱን ስናይ፣ አስደንጋጭ ነው ። የቤተሰብ ሕጋችን ሊፈተሽና ማስተካከያ ሊደረግበት የሚገባ እንደሆነም አመላካች ነው።

በተለይ የጭማሪ መጠኑ በዚህ ልክ በመሆኑ አስደንግጦኝ መፍትሔ ይበጅለት አልኩኝ እንጂ፣ በየሰፈሩ እዚህ ግባ በማይባል ምክንያት ትዳር ፈርሶ የተለያዩ ከፍተኛ ማኅበራዊ ችግሮች ሲያስከትል ታዝባለሁ። በተለይ ከተፋቺዎቹ አብራክ የተገኙ ሕጻናት የፍቺው ቀጥተኛ ተጎጂ ሆነው ሲሰቃዩም አስተውያለሁ።

ትዳር የተቀደሰና ክቡር ነው። በሰከነ አዕምሮ አሰላስሎ የሚገቡበት እንጂ፣ እንጣጥ ብለው የሚገቡበት እንዲሁም እንጣጥ ብለው የሚወጡበት መሆን አይገባውም። በየትኛውም የኢትዮጵያ አካባቢ ትዳር ልክ እንደሕንድ ሁሉ ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠው ነው። ታዲያ በሚያስደነግጥ ሁኔታ ፍቺ በኢትዮጵያ እየጨመረ መምጣቱ ምክንያቱ ምንድን ነው?

ብዙ ምክንያት መጥቀስ የሚቻል ቢሆንም፣ እንደእኔ ዕይታ በኢትዮጵያ ፍቺ እየጨመረ የመጣበት ዋና ምክንያት ወደ ትዳር ለመግባት መግቢያው በር ሰፊ መሆኑ ይመስለኛል። አንድ ሰው 18 ዓመት ከሞላው/ከሞላት/ ምንም አይነት አስገዳጅ መስፈርት ሳያስፈልግ ጋብቻ በማድረግ ትዳር ውስጥ መግባት ይችላል/ትችላለች። ተዋደናል በማለትም ጋብቻ ሳይፈጽሙ "ትዳር አከል" ኑሮ ማድረግም ይቻላል፤ ይህንንም "ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር"(ትዳር) በሚል ሕጉ ፈቃድ ሰጥቶታል።(የቤተሰብ ሕጉን አንቀጽ 98 ይመልከቱ)።

ይህን የመሰለ ወደ ጋብቻ ለመግባት ያለው ሰፊ በር ትዳርን ሁሉም እንዲሞክረው ያደረገው ይመስለኛል። ትዳር የሚሞከሩት ሳይሆን የሚኖሩት ሕይወት ነው። በትዳር አብሮ ለመኖር ብዙ ነገር ይጠይቃል። በአብዛኛው የፍቺ መንስኤ ከዝግጅት ማነስ ጋር ሊያያዝ ስለሚችል÷ ስለጋብቻ፣ ቤተሰብ አስተዳደር እንዲሁም ከራስ ይልቅ ለሌላ ሰው መኖርን በንባብና በሌሎች ዘዴዎች ሰዎች ራሳቸውን ቢገነቡ(ቢያዘጋጁ) የፍቺ መጠንን ለመቀነስ እንደሚያግዝ የጋብቻና የቤተሰብ አማካሪዎች ያስረዳሉ።

ለፍቺ መብዛት ሌላው ምክንያት የሚመስለኝ አንድ ሰው ከትዳር መውጣት ሲፈልግ እንደመግቢያው ሁሉ በሩ ሰፊ መሆኑ ነው። ለመግቢያው እንኳን 18 ዓመት መሙላትን እና ሌሎች ነገሮችን እንደመስፈርት አስቀምጧል። ከትዳር ለመውጣት ግን ሕጉ ያስቀመጠው መስፈርት ለፍርድ ቤት የፍቺ ጥያቄ ማቅረብ ነው። የፍቺ ጥያቄ ሲቀርብ ለመፋታት የወሰኑበትን ምክንያት እንኳን ለመግለጽ አይገደዱም። (አንቀጽ 76 እና 77 ይመልከቱ)

በቤተሰብ ሕጉ ለፍርድ ቤት የተሠጠውን ሥልጣን ስንመለከት፣ የትዳር ፍቺ ጥያቄ ሲቀርብ ፍርድ ቤቱ ሀሳባቸውን እንዲለውጡ ይጠይቃል፤ ሀሳባቸውን የማይለውጡ ከሆነ እንደነገሩ ሁኔታ ከሦስት ወር የማይበልጥ የማሰላሰያ ጊዜ በመወሰን ሊያሰናብታቸው ይችላል። ለተጋቢዎቹ የተወሰነው የማሰላሰያ ጊዜ ካበቃበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የፍቺ ውሳኔ ይሰጣል የሚል ድንጋጌ እናገኛለን። (ከአንቀጽ 78 እስከ አንቀጽ 82 ይመልከቱ)

ከላይ እንደተመለከትነው ዳኛው የፍቺ ጥያቄው በቀረበለት በአጭር ጊዜ ውስጥ ውሳኔ እንዲሰጥ ይጠበቅበታል። ይህ አጭር ጊዜ ትዳር የማፍረስ ሩጫ ነው!!! ትዳርን የሚያክል የተቀደሰና የተከበረ ተቋም ለማፍረስ ሩጫው ለምን አስፈለገ?!

"የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ለመገንዘብ የሚረዱ አንዳንድ ነጥቦች" በሚል ርዕስ የሕግ ምሑሩ መሓሪ ረዳዒ በጻፉት መጽሐፍ፣ ሕጉ በዚህ መልኩ እንዴት እንደወጣ ረቂቁ ሲዘጋጅ አባል ስለነበሩ ምክንያቱን አብራርተዋል። በወቅቱ ሕጉ እንዲወጣ ያስፈለገበት ምክንያት ቢኖርም እንኳን አሁን ያለው ነባራዊ ሁኔታ ለትዳር እጅግ ከፍተኛ ጥበቃ የሚያስፈልግበት ወቅት በመሆኑ ሕጉ ዳግም ሊፈተሽ ይገባል ብለዋል።

የሕንድ የቤተሰብ ሕግ ለትዳር የሚሰጠውን ያህል ጥበቃ፣ የቤተሰብ ሕጋችን ለምን ጥበቃ አያደርግም?! ቀደም ሲል በነበረው የቤተሰብ ሕግ በቀላሉ ፍቺ መፈጸም አይቻልም ነበር፤ ረቂቁም ላይ ፍቺን በቀላሉ መፈጸም እንዳይቻል ተደርጎ እንደነበርም የሕግ ባለሙያው በመጽሐፋቸው አመልክተዋል።

እንደኔ እንደኔ ከሆነ ግን የትዳር ጥበቃው አንድም ወደ ትዳር ሲገባ፣ አንድም ከትዳር ሲወጣ ሊሆን እንደሚገባ ይሰማኛል ። ለምሳሌ ትዳር ሲመሠረት፣ ቤተሰብ ለማስተዳደር የሚያስችል የንቃተ-ሕሊና ማዳበሪያ ኮርስ በማዘጋጀት ኮርሱን ወስዶ ማጠናቀቅ ለሁለቱም ተጋቢዎች ግዴታ ቢሆን እላለሁ። ምክንያቱም በአብዛኛው የፍቺ መንስኤ ወደትዳር ለመግባት ከሚደረግ ዝግጅት ማነስ ጋር ሊያያዝ ስለሚችል ነው።

ጋብቻ ለማፍረስ የሚመጣ ባለትዳር ደግሞ ወደፍርድ ቤት ከመምጣቱ በፊት ጋብቻ ሲፈርስ ምን አይነት ጉዳቶች ለራስ፣ ለልጆች፣ ለቤተሰብ እና ለሀገር ሊያስከትል እንደሚችል የግንዛቤ ማዳበሪያ ኮርስ በመስጠት ኮርሱን ማጠናቀቅ እንደግዴታ ተወስዶ ቢተገበር መልካም ነው። የጋብቻ ፍቺ ጥያቄ ወደ ፍርድ ቤት ይዞ የሚመጣ ባለትዳር ጉዳዩን በቅድሚያ በሽምግልና እንዲያሳየው እንደአስገዳጅ መስፈርትነት ማስቀመጥን ጨምሮ ሌሎች በጣም አሳሪ ያልሆኑ፣ ነገር ግን ትዳርን ሊጠብቁ የሚችሉ መስፈርቶች በመመካከር በሕግ አግባብ ማበጀት ይቻላል።

ይህን አይነት መስፈርት ማስቀመጥ ማስፈለጉ ትዳር የተከበረ ተቋም ከመሆኑ አንጻር ጥበቃ ሊደረግለት ስለሚገባ ነው። አሁን ባለው ሁኔታ የቤተሰብ ሕጋችን ወደ ትዳር የመግቢያውን ሆነ የመውጫው በር ሰፊ ማድረጉ እንደ ሀገር እያስከተለ ያለው ቀውስ አሳሳቢ እየሆነ ነው፣ ከወዲሁ መፍትሔ ካልፈለግንለት ችግሩ የከፋ እንደሚሆን መገመት አይከብድም።

ከዚህ የተነሳም ፍቺን በተመለከተ የተቀመጡ አንቀጾችን ትኩረት ሰጥቶ በመመልከት ሊሻሻሉ የሚገባቸውን አንቀፆች ፈጥኖ ማሻሻል ያስፈልጋል። ይህን ማድረግ ካልቻልን ዛሬ ላይ በየዓመቱ እየተስተዋለ ያለው 60 በመቶ የፍቺ እድገት፣ የዛሬ አምስት ወይም 10 ዓመት የት ሊደርስ እንደሚችል መገመት አይከብድም።

የትዳር መፍረስ በቅድሚያ እየጎዳ ያለው ሀገር ተረካቢ የሆነውን ትውልድ ነው፤ ስለሆነም ትዳርን በአግባቡ በመጠበቅ ትውልዱን፣ ቤተሰብን እና ሀገርን እንጠብቅ፣ ይህ ደግሞ የዚህ ትውልድ ኃላፊነት ነው እላለሁ።

ኢኮኖሚ

# ንግድና ግብይት

# አምራቾችንና ሸማቾችን ያለ ደላላ ያስተሳሰረ መድረክ

ፍሬሕይወት አወቀ




ሁለተኛው ዓለም አቀፍ የማዕድንና ቴክኖሎጂ ኤክስፖ በሚሊኒየም አዳራሽ በቅርቡ መካሄዱ ይታወቃል። በኤክስፖው ላይ ሀገሪቱ በማዕድን ሀብት ባለጸጋ መሆኗን በሚገባ ያመላከቱ በርካታ የማዕድን ዓይነቶች ለእይታ ቀርበዋል። የወርቅ፣ የድንጋይ ከሰል፣ የብረት፣ እንደ ኦፓል ያሉ የከበሩ ማዕድናት በተለያዩ ኩባንያዎች ቀርበው ተጎብኝተዋል። ለመስታወት፣ ለብርጭቆ፣ ለሴራሚክ እቃዎች እንዲሁም ለሲሚንቶ ፋብሪካዎች ግብዓት የሚሆኑ ልዩ ልዩ ማዕድናትም በኤክስፖው ከቀረቡት መካከል ይጠቀሳሉ።

በመድረኩ በኩባንያዎችና በማህበራት የቀረቡ የማዕድን ናሙናዎች ዓይነትና ብዛት የቀረቡበትን መንገድ በተመለከተ የማዕድን ሙዚየም የገባ ያህል ሊሰማው ይችላል፤ ናሙናዎቹ በራሳቸው የሚያስገነዝቡት እንዳለ ሆኖ፣ በምስልና በጽሑፍ የቀረቡ መረጃዎች እንዲሁም በየኩባንያዎቹ፣ ማህበራቱ፣ ወዘተ የተሰጡ ማብራሪያዎች የሀገሪቱን እምቅ የማዕድን ሀብትና ያንን ለማልማት እየተደረጉ ያሉ ጥረቶችን የሚያስገነዝቡ ናቸው።

ከኅዳር 14 እስከ ኅዳር 18 ቀን 2016 ዓ.ም በተካሄደው በዚህ የማዕድንና ቴክኖሎጂ ኤክስፖ ላይ አጠቃላይ ከ90 በላይ ኩባንያዎች፣ ማህበራት፣ ወዘተ መሳተፋቸውን መረጃዎች ያመለክታሉ። በስፍራው ተገኝተን ያነጋገርናቸው ተሳታፊዎች እንደገለጹት፤ በመድረኩ የተገኙት የማዕድናት አልሚ ኩባንያዎች፣ ለኩባንያዎች ግብዓት አቅራቢዎች፣ ገዥዎች የማዕድን ዘርፉ ቴክኖሎጂ አቅራቢ ኩባንያዎች፣ የክልል የማዕድን ቢሮዎች፣ በከበሩ ድንጋዮች ጌጣጌጥ የሚያመርቱ እንዲሁም እነዚህን ጌጣጌጦች የሚሸጡ ማህበራት፣ ወዘተ. ኤክስፖው ምርቶቻቸውንና አገልግሎቶቻቸውን ለማስተዋወቅ አስችሏቸዋል።

ተሳታፊዎቹ መድረኩን ትስስር ለመፍጠሪያነት ወይም ደንበኛ ለማፍሪያነት፣ ልምድ ለማጎልበቻነት፣ ቴክኖሎጂና እውቀት ለማሸጋገሪያነት ተጠቅመውበታል። ጥራት ያለው ምርት ለማምረት የሚያስችል ልምድ ለመጋራት እንዳስቻላቸውም ተናግረዋል። አብረው ለመሥራት ፍላጎት ያደረባቸው ጎብኚዎች ያጋጠሟቸው ኩባንያዎች ስለመኖራቸውም እነዚሁ ተሳታፊዎች ገልጸዋል። ተሳታፊዎቹ ኤክስፖው በቀጣይም ይበልጥ በተጠናከረ መልኩ እንዲካሄድም ጠይቀዋል።

የዘንድሮው መድረክ ከአምናው የተለየ መሆኑም ተጠቁሟል። የዘርፉ መልካም እድሎች፣ ፈተናዎችና መፍትሔዎች የተመላከቱባቸው ሲምፖዚየሞችም ከመድረኩ ጎን ለጎን ተካሂደው ውይይቶች ተደርገውበታል፤ ይህም መድረኩን የተለየ ካደረጉት መካከል አንዱ ነው።

የሀገር ውስጥ ማርብሎችን ከዋናው ከማዕድኑ ጀምሮ እስከ አለቀለት ምርት ድረስ የሚያቀርበው ሳምዳጀ ማርብልና ግራናይት ከእነዚህ ድርጅቶች አንዱ ነው። ያነጋገርናቸው የድርጅቱ ፕሮዳክሽን ማናጀር አቶ ዮናታን የምስራች እንዳሉት፤ ድርጅቱ ላይምስቶን እና ግራናይትን እያመረተ ለገበያ ማቅረብ ከጀመረ 10 ዓመታትን አስቆጥሯል፤ ማዕድኑን ወይም ዋናውን ጥሬ ዕቃ ከአቅራቢዎች በመረከብ ቃሊቲ በሚገኘው ማምረቻው እሴት ጨምሮ ለተለያዩ አገልግሎቶች እንዲውል አድርጎ ያመርታል።

ግራናይት ለደረጃ መወጣጫ እንዲሁም ለሌሎች በርካታ አገልግሎቶች የሚውል ነው። ጥሬ ድንጋዩን ቆርጦ፣ አጥቦና ለሚፈለገው አገልግሎት በሚውል መልኩ ለገበያ የሚያቀርበው ድርጅቱ፣ በሀገሪቱ ከሚገኙ ትላልቅ ፕሮጀክቶች ጋር ትስስር በመፍጠር ለገበያ ያቀርባል። በአብዛኛው ከኮንስትራክሽን ኩባንያዎች ጋር እንደሚሰራ ነው አቶ ዮናታን የተናገሩት።

ኤክስፖው መዘጋጀቱ ድርጅቱን ከተቋራጮች ጋር በማስተዋወቅ የገበያ ትስስር ለመፍጠር እንደሚያስችል ጠቅሰው፣ ኤክስፖው ዓለም አቀፍ ኤክስፖ እንደመሆኑ በተለይም ከውጭ ድርጅቶች ጋር የመተዋወቅ ዕድል እንደሚፈጥርላቸው አስታውቀዋል። ሀገር ውስጥ ካሉና ተመሳሳይ ሥራ ከሚሰሩ ድርጅቶች ጋርም እንዲሁ የመተዋወቅ፣ የልምድ ልውውጥ በማድረግ ጥራት ያለው ምርት ማምረት የሚያስችላቸውን አጋጣሚ እንደሚፈጥርላቸው ነው ያመላከቱት።

እሳቸው እንደተናገሩት፤ ኢትዮጵያ እምቅ የማዕድን ሀብት ያላት ቢሆንም በአግባቡ አልምቶ መጠቀም ላይ ገና ብዙ የሚቀሩ ሥራዎች አሉባት። ዓለም አቀፍ ኤክስፖዎች ሲዘጋጁ የማዕድን ሀብቱን የበለጠ ለመጠቀም ያበረታታሉ፤ በተለይ ሀገሪቷ ወደ ሀገር ውስጥ በምታስገባቸው በርካታ ሸቀጦች ምክንያት የምታጣውን የውጭ ምንዛሪ ለማስቀረት የማዕድን ልማት ወሳኝና ቁልፍ ሚና አለው። ከዚሁ ጋር በተያያዘም ኤክስፖው መንግሥትን ጨምሮ በማዕድን ዘርፍ የተሰማሩ አካላትን በሙሉ ያገናኘ በመሆኑ ለገበያ ትስስር ከሚፈጥረው ዕድል በተጨማሪ በርካታ ጠቀሜታዎችም አሉት።

በመድረኩ ከሚገናኙ አካላት መካከል አምራችና ገዢ ቀዳሚዎቹ ናቸው ያሉት አቶ ዮናታን፣ መድረኩ አምራችና ሸማቾችን ከደላላ ውጭ በቀጥታ ማገናኘት ችሏል ሲሉም አስታውቀዋል። ማዕድን የሚያቀርቡና የሚያወጡ ከአምራቹ ጋር በቀጥታ መገናኘት የቻሉበት መሆኑን ጠቅሰው፣ መንግሥትም በዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን ከባለድርሻ አካላት ጋር ተቀራርቦ መረዳት የቻለበት ሁኔታ ተፈጥሯል ብለዋል። በማዕድን ዘርፉ ያለውን ግንዛቤ ለማስፋት መሰል ኤክስፖዎችን ማዘጋጀትና የማዕድን ዘርፉን ማሳደግ ለዘርፉ ዕድገት የሚኖረው ጠቀሜታ እጅግ የላቀ እንደሆነ አመላክተዋል።

ከሰሜን ሸዋ መራቤቴ አካባቢ ከሚገኘው ኤምኤኬ ትሬዲንግ በኤክስፖው ላይ የሲልካ ሳንድ ወይም የሲልካ አሸዋ ይዞ ተገኝቷል። የድርጅቱ የሽያጭ ሠራተኛ አቶ ዘላለም ደምሴ ሲልካ አሸዋ ለመስታወት፣ ለብርጭቆና ለመሳሰሉት ዋና ግብዓት መሆኑን ይገልጻሉ፤ በተጓዳኝም ለቀለም፣ ለኮንስትራክሽን ግብዓትነትና ለሴራሚክ ማምረቻነትም እንደሚጠቀም ገልጸዋል።

ድርጅቱ በእዚህ ሥራ ላይ አምስት ዓመታትን ማስቆጠሩን የገለጹት አቶ ዘላለም፤ በወር አምስት ሺ ቶን የማምረት አቅም እንዳለውም ጠቅሰዋል። ድርጅቱ ለመስታወት፣ ለብርጭቆ፣ ለቀለም፣ ለሴራሚክ ፋብሪካዎች ለሚገኙበት አዲስ አበባን ጨምሮ ደብረብርሃን፣ ዱከም፣ ደብረዘይትና በሌሎች ከተሞችም ምርቱን እያቀረበ ይገኛል። በሀገር ውስጥ ያለውን የምርት ፍላጎት ማሟላት መቻሉን ጠቅሰው፣ ገበያው ውስን እንደሆነም አቶ ዘላለም ተናግረዋል።

ኤክስፖው መዘጋጀቱ ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለውና በሚገባ እንደተጠቀሙበትም አስረድተዋል። ለሁለተኛ ጊዜ የተዘጋጀው ዓለም አቀፍ የማዕድንና ቴክኖሎጂ ኤክስፖ የውጭ ገበያ ዕድል እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታ እንደፈጠረላቸውም አስታውቀዋል። በተለይ ለድርጅታቸው የውጭ ገበያ ትስስር እንደፈጠረላቸው የጠቀሱት አቶ ዘላለም፤ ከኤክስፖርት ኤጀንቶችና አብረው ሊሰሩ ከሚችሉ ሌሎች ከውጭ የመጡ ባለሀብቶችና ከኤክስፖርተሮች ጋር የመተዋወቅ ዕድል እንደፈጠረላቸውም አመልክተዋል። በዚህም ትልቅ የገበያ ትስስር እንደፈጠሩ፣ ምርቶቻቸውን ሊወስዱላቸው የሚችሉ ገዢዎችን እንዳገኙ ነው ያስታወቁት።

ሲልካ ሳንድ ወይም ሲልካ አሸዋ በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በስፋት እንደሚገኝ ጠቅሰው፣ በእሳቸው አካባቢም በበቂ መጠን እንደሚገኝ ይናገራሉ። ድርጅታቸው ሁለት ፈቃዶች በማውጣት ምርቱን በሁለት ቦታዎች ላይ እያመረተ መሆኑንም ጠቁመዋል። እሳቸው እንዳሉት፤ አንደኛው ማምረቻ በሰሜን ሸዋ መራቤቴ አካባቢ እንሳሮ ወረዳ ይገኛል፤ የማምረቱ ሥራም በ12 ሄክታር መሬት ይከናወናል። ሁለተኛውም እዚያው መራቤቴ ወረዳ የሚገኝ ሲሆን፣ የማምረቱ ሥራም በ12 ሄክታር መሬት ላይ እየተከናወነ ነው።

ድርጅቱ በቋሚና በጊዜያዊ 450 ለሚደርሱ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠሩንም አቶ ዘላለም ጠቅሰዋል። በቀጣይም የማምረትና የገበያ ተደራሽነቱን የማስፋት ዕቅድ እንዳለው ተናግረው፣ በተለይም ምርቱን በጥራትና በስፋት አምርቶ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ማቀዱንም አስታውቀዋል። አቅሙን ይበልጥ በማሳደግና እሴት በመጨመር የመስታወትና የብርጭቆ ፋብሪካ የመገንባት ዕቅድ እንዳላቸውም አመልክተዋል። ብርጭቆና መስታወት ለማምረት ሲልካ አሸዋ 75 በመቶ፣ ሶዳሽ 10 በመቶ፣ ላይም ስቶን 15 በመቶ እንደሚያስፈልግ ገልጸው፣ 90 በመቶ ግብዓት በሀገር ውስጥ ሊሸፈን እንደሚችል አስታውቀዋል።

በኢትዮ ደላንታ ኦፓል እና የከበሩ ማዕድናት ኤክስፖርት ድርጅት ውስጥ ተቀጥራ የምትሰራው ወጣት ሰፊ አዳነ፤ የኦፓል ምርቶችን እንዲሁም ከሌሎች የከበሩ ማዕድናት የተዘጋጁ በርካታ ጌጣጌጦችን ይዛ ነው በኤክስፖው ላይ የተገኘችው። ድርጅቱ የጌጣጌጥ ምርቶቹን ለገበያ እንዲሁም ለማስተዋወቅ ነው ይዞ መቅረቡንም ገልጻለች።

በወሎ ደላንታ በስፋት የሚገኙትን እንደ ኦፓል፣ አማዞናይት፣ ብላክ ኦፕሲዲያ፣ አማቲስትና ሌሎች ጌጣጌጦችን ይዛ እንደቀረበች ጠቅሳ፣ ማዕድናቱ እጅግ ተፈላጊ እንደሆኑ ትናገራለች። ጌጣጌጦቹን ለማምረት አስፈላጊ የሆኑ የማዕድን ዓይነቶችን ከአቅራቢዎችና ከነጋዴዎች ገዝቶ እንደሚያመርት ገልጻለች።

ድርጅቱ ጌጣጌጦችን አምርቶ ለሀገር ውስጥ ገበያ ከማቅረብ ባለፈ የከበሩ ድንጋዮችን በጥሬው ለውጭ ገበያ እንደሚያቀርብ ተናግራለች። ምርቶቹ በስፋት የሚላኩት ወደ ህንድ መሆኑንም አጫውታናለች። እሷ እንዳለችው፤ እንደ ደንበኞች ፍላጎትም እሴት የተጨመረባቸውንና ፖሊሽ የተደረጉ ምርቶችን ድርጅቱ ለገበያ ያቀርባል። ከዚህም ባለፈ ምርቶቹን ወደ ጌጣጌጥነት በመቀየር ለመዋቢያና ለጌጣጌጥነት እንዲውሉ እያደረገ መሆኑን ጠቅሳ፣ እነዚህ ምርቶች ሰፊ ገበያ እንዳላቸውም ጠቁማለች። ምርቶቹ በወሎ ደላንታ የሚዘጋጁ ሲሆን፣ በአዲስ አበባ ደግሞ የመሸጫ ሱቅ አለው።

እሷ እንዳለችው፤ ጌጣጌጦቹ የአንገት፣ የጆሮና የእጅ መዋቢያና ማጌጫ ናቸው። ከዚህ ቀደም ማህበረሰቡ ለከበሩ ድንጋዮች ዝቅተኛ አመለካከት ነበረው፤ ይህ አመለካከት አሁን እየተቀየረ መጥቷል። ምርቶቹን በስፋት የመጠቀም አዝማሚያ እየታየ ነው።

በማህበረሰቡ ዘንድ እየታየ ያለው ይህ ለውጥ የመጣው በተለያየ ጊዜ በሚዘጋጁ ኤክስፖዎች ምርቶቹን አውጥቶ ማስተዋወቅ በመቻሉ ነው። ኤክስፖው የገበያ ዕድሎችን የሚፈጥርና ምርቶቹን ለማህበረሰቡ ብሎም ለውጭ ገዢዎች ለማስተዋወቅ የሚያስችል እጅግ ጠቃሚ መድረክ መሆኑን አስታውቃለች።

ከዚህ ቀደም በማህበረሰቡ ዘንድ የከበሩ ድንጋዮችን በማውጣት አልምቶ የመጠቀም ባህሉ የዳበረ ካለመሆኑ ጋር ተያይዞ አብዛኛው ማህበረሰብ የከበሩ ማዕድናት ማልማት ላይ ፍላጎት እንዳልነበረው ወጣት ሰፊ ገልጻለች። በወሎ ደላንታ በስፋት የሚገኘውን የኦፓል ማህበረሰቡ አልምቶ እንዲጠቀም በማድረግ በኩል ሜዳ እምርታ የተሰኘው የካናዳ ድርጅት ፕሮጀክት አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑን ተናግራለች። ፕሮጀክቱ ለዘርፉ ዕድገት ትልቅ አበርክቶ እንዳለው ጠቅሳ፣ በዚሁ ምክንያት ወደ ሥራ የገቡ በርካታ ቁጥር ያላቸው ዜጎች መሆናቸውንም ነው ያመለከተችው።

የማዕድን ሚኒስቴር ሚኒስትሩ ኢንጂነር ሀብታሙ ተገኝ በመድረኩ ላይ እንዳሉት፤ ማዕድን ብዙ ነገር ነው። ማዕድን ግብርና ነው፤ በሀገሪቱ የአፈር ማዳበሪያን ማምረት ካልተቻለ ግብርና ዘላቂነት አይኖረውም፤ የምግብ ዋስትናን በዘላቂነት ማረጋገጥም አይቻልም። ማዕድን ኮንስትራክሽን ነው፤ ያለ ሲሚንቶና ብረት ዘላቂ የሀገር ግንባታን ለማስቀጠል ቀላል አይሆንም። ማዕድን ኢንደስትሪ ነው፤ ማዕድን የውጭ ምንዛሪ ግኝት ዋነኛ መሠረት ነው፤ የወጪና ገቢ የንግድ ሚዛን ካልተጠበቀ ዘላቂ የሆነ ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን ማረጋገጥ አይቻልም።

መንግሥት ይህንኑ በመረዳት ከቀደሙት ጊዜያት በተሻለና በተለየ መንገድ ለማዕድን ዘርፉ ልዩና ከፍተኛ የሆነ ትኩረት መስጠቱን ሚኒስቴሩ ተናግረዋል። ኤክስፖው ኢትዮጵያ ያላትን የማዕድን ሀብት ለማስተዋወቅ ፋይዳው ከፍተኛ መሆኑን አመልክተው፣ ባለሀብቶች ያለውን ሀብት ተመልክተው ወደ ሥራ እንዲገቡ የሚያስችል መሆኑንም ገልጸዋል።

"የማዕድን ሀብታችን የነገ ተስፋችን" በሚል መሪ ሃሳብ በሚሊኒየም አዳራሽ የተዘጋጀውን ሁለተኛውን ዓለም አቀፍ የማዕድንና ቴክኖሎጂ ኤክስፖ በንግግር የከፈቱት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እንዳሉት፤ ሀገሪቷ በሁሉም አካባቢዎቿ እጅግ አስደናቂ የሆኑ የማዕድን ሀብቶች ያሏት በመሆኑ ኤክስፖው ለተመራማሪዎችና ኢንቨስተሮች በዘርፉ ምን ዓይነት ሀብት እንዳለ ለማወቅ ዕድል ይፈጥራል። ኢትዮጵያን ከድህነት ለማውጣት በፈተና ጊዜም ቢሆን ችግሮችን ተቋቁሞ ማልማት ይገባል።

ሀገሪቱን ከታሰበው የእድገት ደረጃ ላይ ለማድረስ የኢትዮጵያ የግሉ ዘርፍ በግል ማምረትና ኢንቨስት ማድረጉን አቁሞ በጋራ መሥራት የሚቻልበትን እውቀት የሚሰባሰብበትን፣ ብልጽግና የሚመጣበትን መንገድ መፍጠር እንዳለበትም ጠቅላይ ሚኒስትሩ አስገንዝበዋል። ከችግር ነጻ የሆነ የመልሚያ መንገድ እንደሌለም ጠቅሰው፣ በዘርፉ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በጋራ በመፍታት ወደ ብልጽግና ከፍታ መገስገስ እና ለተተኪው ትውልድ የተሻለች ኢትዮጵያን ማስረከብ እንደሚገባም አስታውቀዋል።

# ግለኝነትን ያነገሱ ማህበራዊ ሚዲያዎች

**አስናቀ ፀጋዬ**

በጊዜ ሂደት የሰዎች የአኗኗር ሁኔታ በሁለንተናዊ መልኩ እየተቀየረ መጥቷል። ይህ ክስተት ዓለም አቀፋዊ ነው። ለሰዎች የኑሮ ሁኔታ በሁለንተናዊ መልኩ መቀየር በርካታ ምክንያቶች አስተዋጽኦ አድርገዋል። ለአብነትም የፖለቲካዊና ማህበራዊ ሕይወት በየጊዜው መለዋወጥ፣ የኢኮኖሚ እድገት፣ የፈጠራ ውጤቶች ማደግና መሻሻል፣ ቴክኖሎጂ፣ ሳይንስና ምርምር ሌሎችም ይጠቀሳሉ።

በተለይ ደግሞ በየዘመኑ የመጡ ሕይወትን የሚያቀሉ ልዩ ልዩ የፈጠራ ውጤቶችና ዘመኑን የዋጁ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ለሰዎች አኗኗር መለወጥ ትልቅ ሚና ተጫውተዋል። ሚዲያውም በራሱ በጊዜ ሂደት መልኩን እየቀያየረ መምጣቱና አዳዲስና በህብረተሰቡ ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ተፅእኖ የሚያሳደሩ መረጃዎችን በገፍ መልቀቁ በሰዎች አኗኗር ላይ የማይናቅ ተፅእኖ አሳድሯል።

አሁን አሁን ደግሞ የማህበራዊ ሚዲያዎች በስፋት መምጣት ዓለምን አቀራርቧል። በዚህም ዓለም ወደ ትንሽ መንደር ተቀይራለች። ይህም ማለት በግሎባላይዜሽን /ሉዓላዊነት/ የዓለም ሕዝብ ማህበራዊ ሚዲያዎች በሚያቀርቧቸው መረጃዎች ተቀራርቧል። አኗኗሩም በሁለንተናዊ መልኩ ተቀይሯል።

ዛሬ በማህበራዊ ሚዲያ አማካኝነት ከየትኛውም የምድር ጫፍ ሆኖ መረጃ ማግኘትና መላክ ቀላል ሆኗል። መረጃ ደግሞ በብዙ መልኩ ጠቀሜታው የጎላ በመሆኑና በሰዎች ሕይወት ላይ ቀላል የማይባል ተፅእኖ ስላለው ከጦር መሳሪያ እኩል ትልቅ ኃይል ሆኗል። በማህበራዊ ሚዲያ መረጃዎች አማካኝነት ፖለቲካን፣ ማህበራዊ ሕይወትንና ኢኮኖሚን እንደየራስ ፍላጎትና ጥቅም መቃኘት ተችሏል። በዚህም ማህበራዊ ሚዲያዎች በሰዎች አኗኗርና ሕይወት ላይ በጎ ተፅዕኖ አሳድረዋል፤ እያሳደሩም ይገኛሉ።

ማህበራዊ ሚዲያዎች በሰዎች ሁለንተናዊ ሕይወት ላይ እያሳደሩ ያሉትን በጎ ተፅዕኖ ያህል አሉታዊ ተፅዕኖዎቻቸውም የዛኑ ያህል እያደገ መጥቷል። በማህበራዊ ሚዲያዎች በሚቀርቡ መረጃዎች አማካኝነት ሰዎች ሕይወታቸውን የመቀየራቸውን ያህል በነዚሁ ሚዲያዎች በሚወጡ የተዛቡ መረጃዎች ወደ ግጭትና አለመግባባት እየገቡ ነው። የራስን ማንነትና ባህል ለቆ የሌላውን መያዝ፣ በጎ አመለካከትን ባልሆነ መቀየርና.... ወዘተ ሌሎችም ይኸው ማህበራዊ ሚዲያው በሰዎች ላይ የፈጠረው በጎ ያልሆነ ተፅዕኖ ነው።

ከዚህ በተጨማሪም ማህበራዊ ሚዲያዎች ለማህበረሰቡ መረጃ ከመስጠት ባሻገር የመዝናኛ አማራጮችንም ፈጥረዋል። በዚህም በርካቶች ውስን ከነበረው የመዝናኛ አማራጭ ወጥተው እንደ እድሜያቸው፣ እንደፆታቸው፣ እንደእምነታቸው፣ እንደየራሳቸው ፍላጎትና ምርጫ እንዲዝናኑ እድል ተፈጥሮላቸዋል። የዛኑ ያህል ደግሞ ሰዎች ይህን መሠረት ባላደረገ መልኩ በማህበራዊ ሚዲያ የሚቀርቡ መዝናኛዎችን ያለምርጫና ያለገደብ መጠቀማቸው ያልሆነ ሁኔታዎች ውስጥ ከቷቸዋል።

ማህበራዊ ሚዲያዎች በአብዛኛው እያንዳንዱ ሰው በራሱ ተንቀሳቃሽ ስልክ፣ ላፕቶፕ አልያም ደግሞ ኮምፒዩተር አማካኝነት የሚጠቀማቸው በመሆኑ ከሌሎች ሰዎች ጋር መነጋገርና ማውራትና በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የመወያየት እድሎችን ገድቧል። እንደ ፌስቡክ፣ ዩቲዩብና ቲክቶክ የመሰሉ የማህበራዊ ሚዲያ ውጤቶች መመልከት አንዳንዴ ሱስ እስከማስያዝ ድረስ ስለሚደርሱ በአንድ ቤት ውስጥ ያለ ቤተሰብን እንኳን የመነጋገርና ሃሳብ የመለዋወጥ እድል ያሳጣል። አሁን አሁን እየሆነ ያለውም ይኸው ነው።

ልጆች በአብዛኛው በቪዲዮ ጌሞችና ዩቲዩብ ላይ ተተክለው ነው የሚውሉት፤ ተተክለው ነው የሚያመሹት። ከእናት አባታቸው ጋር ስለትምህርታቸውና ስለቀን ውሏቸው አያወሩም፤ አይነጋገሩም። የሚነጋገሩት ከታብሌት ወይም ከስልክ ጋር ነው። ለብቻቸው እንጂ ከሰው ጋር መሆን አይፈልጉም። እንደ ልጅ አይጫወቱም።

እናትም ብትሆን ስልኳን ይዛ ፌስቡክ፣ ቲክቶክ ወይ ደግሞ ዩቲዩብ ነው የምታየው። ብዙ ጊዜዋን የምታሳልፈው ይህንኑ ማህበራዊ ሚዲያ በማየት ነው። በዚህ መሃል ልጆችን መከታተል፣ ምን ተምረው እንደመጡ መጠየቅ፣ ስለውሏቸው ማውራት የሚባል ነገር የለም። በእናትና ልጅ መካከል የሚደረግ ንግግርና የሃሳብ ልውውጥ ብዙ አይኖርም።

አባትም ቢሆን በላፕቶፕ ላይ ተተክሎ ቤት እንኳን ሳይቀር ሥራውን ነው የሚሰራው። ሥራው ሲሰለቸው ደግሞ ማህበራዊ ሚዲያዎችን መመልከቱ አይቀርም። ቲክቶክ፣ ፌስቡክና ዩቲዩብ ይመለከታል። ይህን ከማድረግ ፈንታ ለልጆቹ ጊዜ አይሰጥም። ለራሱ ብቻ ነው ጊዜ የሚሰጠው። ልጆቹ ምን ተምረው እንደመጡ እንኳን አይጠይቅም። በቃ! ግለኛ ነው።

ይህ እንግዲህ የማህበራዊ ሚዲያዎች በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ምን ያህል ግለኝነትን እየፈጠሩ እንደመጡና ቤተሰብ እርስ በርስ እንዳይነጋገርና ሃሳብ እንዳይለዋወጥ ተፅእኖ እያሳደሩ ስለመምጣታቸው ይጠቁማል። ከቤተሰብ ባለፈ በጎረቤት፣ በሰፈር፣ በአካባቢ፣ በማህበረሰብና በሀገር ላይም ከማህበራዊነት ይልቅ ግላዊነት እንዲነግስ አሉታዊ ተፅእኖ እያሳደሩ ይገኛሉ።

በዛሬ ዘመን ልክ እንደበፊቱ ቡና አፍልቶ፤ ጎረቤት ተጠራርቶ መነጋገር፣ መጫወት፣ ሃሳብ መለዋወጥ የሚባል ነገር እየጠፋ መጥቷል። ቡናው ቢፈላ እንኳን ቡናውን ለመጠጣት ከመጣው ሰው ውስጥ ግማሽ ያህሉ ስልኩን የሚጎረጉር እንጂ የሚጫወትና ሃሳብ የሚያካፍል አይደለም። ሁሉም በየቤቱ የራሱን ሕይወት ነው የሚኖረው።

> **ማ**ህበራዊ ሚዲያዎች ከቤተሰብ ባለፈ በጎረቤት፣ በሰፈር፣ በአካባቢ፣ በማህበረሰብና በሀገር ላይም ከማህበራዊነት ይልቅ ግላዊነት እንዲነግስ አሉታዊ ተፅእኖ እያሳደሩ ይገኛሉ

አሁን አሁንማ በሠርግም በለቅሶም፣ በልደትም በተስካርም ሰው ታዘበኝ አልታዘበኝ ሳይሉ ስልካቸው ላይ አፍጠው ፕሮግራሙ እንዴት እንኳን እንደተካሄደ በቅጡ ሳይረዱ ወደቤታቸው የሚሄዱ ብዙዎች ናቸው። በየመንገዱ ስልካቸውን እየነካኩ ዞር ብለው የማያዩና ለአፍታ እንኳን ቀና የማይሉ ከፖል አልያም ከሰው ጋር የሚጋጩ፤ ወይም ከመጋጨት ለጥቂት የተረፉም በርካታ ናቸው።

እንግዲህ ማህበራዊ ሚዲዎች ይህን ያህል ቀልብ እስከ ማስረሳት የሚያደርስ ተፅእኖ በሰዎች ላይ እያደረሱ ነው። ሰዎች የግለኝነት ባህሪን እንዲላበሱም የማይናቅ አስተዋፅኦ እያበረከቱ ነው። ያ የምንኮራበትን ማህበራዊ ሕይወታችንንም እያናጉ ነው። እና? እናማ የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀማችን በወጉ ይሁን!!

# ዓለም አቀፍ

## ፕሬዚዳንት ፑቲን በአረብ ኢምሬትስና በሳዑዲ አረቢያ ጉብኝት ሊያደርጉ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የሩሲያው ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን በተባበሩት አረብ ኢምሬትስ እና በሳዑዲ አረቢያ ጉብኝት ሊያደርጉ መሆኑ ተገለጸ።

የሩሲያ ፕሬዚዳንት ቤተ መንግሥት ክሬምሊን ቃል አቀባይ እንዳስታወቁት፤ ፑቲን ከዛሬ ጀምሮ ነው ጉብኝታቸውን ማድረግ የሚጀምሩት ተብሏል።


የሩሲያ ፕሬዚዳንት አማካሪ ዩሪ ኡሻቭ፤ ፕሬዚዳንት ፑቲን ጉብኘታቸውን በሳዑዲ አረቢያ እንደሚጀመሩ እና በዚያም ከሳዑዲ ልዑል አልጋ ወራሽ መሀመድ ቢን ሰላመ ጋር ይወያያሉ ብለዋል።

በመቀጠልም ወደ አረብ ኢምሬትስ እንደሚያቀኑ እና በዚያም ይፋዊ የሥራ ጉብኝት እንደሚያደርጉ አማካሪው አስታውቀዋል።

የሩሲያው ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን በሁለቱ ሀገራት የሚያደርጉት ይፋዊ የሥራ ጉብኝት እና ውይይቶች በጣም ወሳኝ እንደሆነም አማካሪው ዩሪ ኡሻቭ አስታውቀዋል።

የሩሲያው ባለስልጣን የፕሬዚዳንት ፑቲን ጉብኝት መቼ እንደሚጀመር ቁርጥ ያለ ቀን ባያስቀምጡም፤ አል ዐይን ኒውስ ከምንጮች ያገኘው መረጃ ነገ እንደሚጀመር ያመለክታል።

በተባበሩት አረብ ኢምሬትስ እና በሳዑዲ አረቢያ በኩል የፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲንን ጉብኝት



ቭላድሚር ፑቲን

አስመልክቶ እስካሁን ይፋዊ መግለጫ አልተሰጠም።

የሩሲያው ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን ዓለም አቀፍ የእስር ማዘዣ ከወጣባቸው በኋላ የውጭ ሀገራት ጉዞን በእጅጉ የቀነሱ ሲሆን፤ አብዛኛውን ጊዜም የቀድሞ የሶቪዬት ህብረት አካል የነበሩ ሀገራትን ብቻ ሲጎበኙ ነበር።

ፑቲን ከእነዚህ ሀገራት ውጭ የመጀመሪያ ጉብኝታቸውን ያደረጉት ባሳለፍነው ጥቅምት ወር በቻይና ነበር።

## የዩቲዩብ ተመልካች ለማግኘት ሆን ብሎ አውሮፕላን የከሰከሰው ዩቲዩበር ተፈረደበት

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አሜሪካዊው ዩቲዩበር የተመልካች ቁጥር ለማግኘት ሲል ሆን ብሎ አውሮፕላን በመከስከሱ እና የአደጋ መርማሪዎችን በመዋሸቱ በስድስት ወራት እስር እንዲቀጣ ተፈረደበት። የ30 ዓመቱ ትሬቨር ጄኮብ አውሮፕላኑ በአደጋ ምክንያት የተከሰከሰ የሚያስመስለውን ተንቀሳቃሽ ምስል ከሁለት ዓመታት በፊት ነበር ዩቲዩብ ላይ የጫነው።

ይህ ቪዲዮ በጉግል ከዩቲዩብ ገጽ እንዲሰረዝ ከመደረጉ በፊት ከሦስት ሚሊዮን ጊዜ በላይ ተመልካችን ለማግኘት ችሎ ነበር። ጥፋቱን ለማመን ከዐቃቤ ሕግ ጋር ባደረገው ስምምነት መሠረት ግለሰቡ ቪዲዮውን የቀረጸው አንድ ምርትን ለማስተዋወቅ በደረሰው ስምምነት ምክንያት መሆኑን አመልክቷል።

የቀድሞ የኦሎምፒክ ተሳታፊ የሆነው ትሬቨር ጄኮብ ንብረት በማውደም እና ከፌዴራል መርማሪዎች መረጃ በመሰወር ወንጀል ጥፋተኛ መሆኑን ከአንድ ዓመት በፊት አምኖ ነበር።

በካሊፎርኒያ ያሉ መርማሪዎች ጄኮብ ይህን ጥፋት የፈጸመው የማኅበራዊ ሚዲያ ተከታዮችን ቁጥር በመጨመር እና እራሱን የዜና ማዕከል በማድረግ የገንዘብ ጥቅም ለማግኘት ነው ብለዋል።

የፍርድ ቤቱን ውሳኔ ተከትሎ ጄኮብ ባወጣው መግለጫ የተላለፈበት ፍርድ “ትክክለኛ ውሳኔ ነው” በማለት በቅጣቱ እንደሚስማማ ገልጿል። ግለሰቡ ከሁለት ዓመት በፊት ከካሊፎርኒያ ሳንታ ባርባራ አየር ማረፊያ ብቻውን በሚያበራት አውሮፕላን ላይ ካሜራዎችን ገጥሞ የተነሳ ሲሆን፣ ካሜራዎችን ይዞ አውሮፕላኗ አየር ላይ እንዳለች በፓራሹት ዘሎ በመውረድ ስትከሰከስ የሚያሳየውን አጠቃላይ ሂደት ቀርጿል።

አውሮፕላኗ ለበረራ ከተነሳች ከ35 ደቂቃዎች



በኋላ ሎስ ፓድሬስ በተባለ ደን ውስጥ ነበር ወድቃ የተከሰከሰችው። “ቀድሞም ቢሆን ከአንድ መዳረሻ ላይ የማረፍ ዕቅድ አልነበረውም። የነበረው ዕቅድ በፓራሹት ከአውሮፕላኑ ዘሎ ሲወርድ እና አውሮፕላኑ ቁልቁል ሄዶ ሲከሰከስ መቅረጽ ነበር” ብሏል የካሊፎርኒያ ዐቃቤ ሕግ።

ከዚያም የኪስ ቦርሳ የሚያመርት ኩባንያ ማስታወቂያን ጨምሮበት “አውሮፕላኔን ከሰከስኩ” በሚል ርዕስ ከሁለት ዓመታት በፊት ዩቲዩብ ላይ ቪዲዮ ጭኗል።ቪዲዮ እንደወጣ አንዳንድ ተመልካቾች ትንሿ አውሮፕላን የተከሰከሰችው ድንገት ባጋጠመ አደጋ መሆኑን ሲጠራጠሩ ነበር።

ጄኮብ ቀድሞውን ፓራሹት አጥልቆ መሳፈሩን እንዲሁም አውሮፕላኗን ከአደጋ ለማዳን ምንም ዓይነት ጥረት አለማድረጉን በመጥቀስ ሆን ብሎ አውሮፕላኗን ከስክሷል ሲሉ ተደምጠው ነበር።

ጄኮብ ክስተቱን ለአሜሪካ የትራንስፖርት ደኅንነት ቦርድ ሪፖርት ያደረገ ሲሆን፣ ባለሥልጣኑም የአውሮፕላኗን ስብርባሪ መሰብሰብ እንዳለበት ሲነገረው አውሮፕላኗ የት እንደወደቀች እንደማያውቅ ገልጾ ነበር ተብሏል።

ከዚያ ግን ወደ አደጋው ስፍራ በሄሊኮፕተር በመሄድ ስብርባሪውን አግኝቶ ከስፍራው እንዲነሳ አድርጎ ማስረጃዎችን ማጥፋቱን የዐቃቤ ሕግ መረጃ አመልክቷል።

# ባለውለታዎቻችን

# በተግባር የተገለጠ ሀገር ወዳድነት

**- ዶክተር በላይ አበጋዝ**

ክብረአብ በላቸው



በእያንዳንዱ የዕውቀት ዘርፍ የሚደረግ ጥናትና ምርምር የሰዎችን ሕይወት ማሻሻል ላይ ትኩረት ያደረገ መሆን እንዳለበት ብዙዎች ይስማማሉ፡፡ አንድ ሰው በትክክል "ምሁር" ለመባል ብቁ የሚሆነው ዕውቀቱን ከራሱ አልፎ በሌሎች ሕይወት ላይ ለውጥና መሻሻል ለማምጣት የሚጠቀምበት ከሆነ ነው፡፡ ምሁርነትም ከዚህ አንፃር ታይቶና ተመዝኖ የሚሰጥ ክብር እንደሆነ ብዙዎች ይናገራሉ።

አብዛኞች እንደዋዛ ጥለዋት በሚለይዋት ዓለም በተቃራኒው ጥቂቶች ከራሳቸው አልፈው ለሌሎች የሚተርፍ አስተዋጽኦ አበርክተው ማለፉ ይሳካላቸዋል። በሚያልፍ ዕድሜ የማያልፍ ሥራ ሠርተው ስማቸው ሲወሳ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን መካከል አንዱ የኢትዮጵያ የልብ ሕክምና ማዕከል መስራች ዶክተር በላይ አበጋዝ ናቸው። ዕውቀት ብስለት ከጥበብ ጋር የሰመረላቸው እና ለኢትዮጵያ ሕፃናት እና ወላጆች ተስፋ የሆኑ ሰው ናቸው።

የኢትዮጵያ የልብ ሕክምና ማዕከል መስራች የሆኑ ዶክተር በላይ፤ በደቡብ ወሎ ኩታበር 1937 ተወልደው፣ ደሴ በሚገኘው ወይዘሮ ስህን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ትምህርታቸውን ተከታትለዋል። በየዓመቱ ከልብ ሕመም ጋር ለሚወለዱ ከ50 እስከ 60 ሺህ ለሚሆኑ ሕፃናት ተስፋ መሆን የቻሉ ሰው ናቸው። ዶክተር በላይ አበጋዝ ከምንም ነገር በፊት ሀገርና ወገንን ያስቀድማሉ፡፡ መነሻቸውን ቅንነትና አገልጋይነት ነው፡፡

በተግባር የተፈተነ የሀገር ፍቅር ያላቸው እኚህ ጉምቱ ኢትዮጵያዊ በአንድ ቃለ ምልልሳቸው ዶክተር ኢትዮጵያዊ መሆን ምን የተለየ ስሜት አለው? የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር፡፡ ሱዳናዊ፣ ኬንያዊ፣ አሜሪካዊ ከመሆን በምን ይለያል? በሚል ለተነሳላቸው ጥያቄ ሲመልሱ እንዲህ ተናግረው ነበር፡፡ እኔ ምን አውቄ ሱዳናዊ ወይም የጠቀስካቸው ሀገሮች ዜጋ ሆኘ አላውቅ። "ሀ" ሲባል ኢትዮጵያዊ ነኝ። ኢትዮጵያዊ ሆኜ መሞትም ነው የምፈልገው። በሕይወቴ የማልክዳቸው ሶስት ለራሴ የገባኋቸው ቃል ኪዳኖች አሉ። ከነሱ አንዷ ሀገሬ ናት ሲሉ ይናገራሉ።

ዶክተር በላይ በተጨማሪ ሲናገሩ፤ ስለ ሀገር ከተነሳ ሌላ አንድ ነጥብ ላንሳልህ ብለው በመቀጠል አንድ ገጠመኛቸውን በዚህ መልኩ አጋርተዋል፡፡ ትልቁ ልጄ ገና ትንሽ ልጅ ሆኖ (በወቅቱ አሜሪካ ነበርን) "ሀገራችን እንሂድ?" አለኝ "ለምን?" አልኩት። " ይሄ ሀገር (አሜሪካ) ልክ አይደለም። ልክ ቢሆን ኖሮ እኔን ስለ አሜሪካ ታሪክ ሲያስተምሩኝ ክፍል ውስጥ ላሉት ደግሞ የኢትዮጵያን ታሪክ ማስተማር ነበረባቸው" አለኝ። በወቅቱ የሱ አዕምሮ ይሄን አሰበ። ሁለት ሳምንት ሳይሞላው ደግሞ ትንሹ ልጄ እናቱን "ወደ ሀገራችን እንሂድ አላት" "ለምን?" ስትለው "ብትሞቺብንስ?" አላት። " እኔ ብሞት በሥርዓት የሚያሳድግ አባት አላችሁ" ብላ መለሰችለት። አስበው በጣም ትንሽ ልጅ ነው።

ዶክተር በላይ በመቀጠል "አባቴስ ቢሞት አላት?" "ለምን ይህን ታስባለህ? አለችው። "ሁለታቹሁም ብትሞቱ ወላጅ አልባ ነው የምንሆነው። ወላጅ አልባ ከሆንን ደግሞ የሀገራችን ሕዝብ እንዲያሳድገን ነው የምንፈልገው።" አላት። አንተ በዚህ ልጅ ወይም በኔ ቦታ ብትሆን ምን ነበር የምትመልሰው? ሰባት ዓመት ያልሞላው ልጄ ገና በአንድ ዓመቱ ለቋት በሄደው ሀገሩና በማያውቃቸው ኢትዮጵያዊያን ላይ እምነቱን እንዲህ ጥሏል። ልክ በሃይማኖት ሳንከራከር እንደምናምነው ኢትዮጵያዊነትንም ሳልከራከር ነው የምቀበለው። ምንም ቢሆን ይህንን ተስፋዬን ማጣትም አልፈልግም። ገንዘቤ ሊወሰድ ይችላል። ጤንነቴ ሊጓደል ይችላል። ተስፋዬን መነጠቅ ግን በፍፁም አልሻም። በማለት መልሰዋል።

ዶክተር በላይ አበጋዝ ሀገራቸውን ያገለገሉት በሕክምና ሙያ ብቻ አይደለም፡፡ የሕይወት መስዋዕትነት በሚያስከፍለው የውትድርና ሙያ ላይም ተሰማርተው የቆዩ ሰው ናቸው። በሐረር ወታደራዊ ትምህርት ቤትም የወታደራዊ ሳይንስ ተምረዋል፡፡ በዚህ ሙያቸውም የሌተናል ኮሌኔልነት ማዕረግ ተቀብለዋል፡፡ ጀግና፤ በጎ አድራጊ፣ ጎበዝ ወታደር ሆነውም በንጉሡ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ አራት ጊዜ ተሸልመዋል።

ዩኒቨርሲቲ ገብተው አጠቃላይ ሕክምናን ካጠኑ በኋላ የልብ ሕክምናን በተለይም የሕፃናትን ልብ ሕክምና በማጥናት አሁን ላይ መሠረት እንዲጣል ለተደረገው የዘርፉ ሕክምና አበርክቷቸው የጎላ እንዲሆን አድርጎታል፤ የሕፃናት ልብ ስፔሻሊስቱ ዶ/ር በላይ አበጋዝ።

ዶክተር በላይ፣ ከራስ ወዳድነት የፀዳ አመለካከት እንዳለቸው የተለያዩ ግለሰቦች ምስክርነታቸውን ይሰጣሉ ከእነዚህ መካከል፤ ምስ ጅዝ ልዘክ የተባሉ ፀሐፊ a man with heart for all children's በተባለ ጽሑፋቸው ዶክተር በላይ አበጋዝ ራስ ወዳድ ያልሆነ ቁሳቁስን ለማጋበስ ፍላጎት የሌለውና ሀገሩን፣ ሕዝቡን የጎረቤት ሀገራትን የልብ ሕመም ሕፃናትንና ወላጆቻቸውን በነፃ የሚያገለግል ሐኪም ነው በማለት ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል።

ዶክተር በላይ አበጋዝን በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ በስፋት ያስተዋወቀቻቸው የልብ ሕሙማን ሕፃናት መርጃ ድርጅት ነው። የልብ ሕመም ያለባቸው ሕፃናት ወደ ውጭ ሀገር ሄደው ለመታከም የሚያስችል አቅም ስለሌላቸው የሚያጋጥማቸውን ጉዳት ለመቀነስ ዶክተር በላይ በመላው ዓለም ዞረው ድጋፍ በማሰባሰብ የመሠረቱት የነገ ሀገር ተረካቢዎች ተስፋ ለሆኑ ሕፃናት የደረሰ ድርጅት ነው። ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያንን፣ የውጭ ሀገር ዜጎችን፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማትን፣ የነፃ ሕክምና አገልግሎት ሰጭ ሐኪሞችንና መሳል ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር ለትውልድ የሚተርፍ ስኬታማ ሥራን ሰርተውበታል።

መላውን የኢትዮጵያ ሕዝብና ባለሀብቶችን በማስተባበር ያቋቋሙት የኢትዮጵያ የልብ ሕክምና ማዕከል ለበርካታ ሕፃናትና የልብ ሕክምና ፈላጊዎች ሕክምናው በስፋት እንዲሰጥና ተደራሽ እንዲሆን የእሳቸው ጥረትና መና ከፍተኛ ነው። በ30 ዓመታት ቆይታውም ከ10ሺህ በላይ ሕፃናት የልብ የሕክምና ተጠቃሚ እንዲሆኑ አስችለዋል። ለአንድ ሕፃን ሕክምና ያስፈልግ የነበረውን የ30ሺህ ዶላር ወጪ፣ የጊዜ ብክነት፣ የወላጆችን እንግልትና ስቃይ ያስቀረ ነው።

ዶክተር በላይ ከሕፃናት የልብ ሕክምና ማዕከሉ በተጨማሪ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስር በዶክትሬት ዲግሪ ፕሮግራም የሚያስተምር፣ ጥናት የሚያደርግ የልብ ሕክምና ኮሌጅ እንዲመሰረት ከማድረጋቸው ባሻገር በሚያስፈልጉት እገዛዎች የተለያዩ ግለሰቦች፣ ሀገራትንና ተቋማትን በማናገር የሕክምና ኮሌጁ በሁለት እግሩ ቆሞ ለኢትዮጵያ ሕፃናት ተገቢውን አገልግሎት መስጠት እንዲችል ከፍተኛ ሚና ተወጥተዋል።

ዶክተር በላይ አበጋዝ በትህትናቸው ይታወቃሉ፡፡ ብዙዎች ጥቂት ሰርተው ብዙ በሚናገሩበት ዘመን አያሌ ለሀገርና ሕዝብ የሚጠቅም ነገር ሰርተው "ገና ምንም አልሰራሁም" የሚሉ ናቸው፡፡ ይህ ስብዕና ብዙዎች ጋር የሌለ ለጥቂቶች የሚሰጥ መልካም ፀባይ ወይም ባህርይ ነው። ዘርፉን ለማጥናት የወሰኑበትን ምክንያት ሲናገሩ "በየዓመቱ ከ50ሺህ በላይ ሕፃናት ከልብ በሽታ ጋር ይወለዳሉ፤ በተጨማሪ ከ50 ሺህ - 60ሺህ ደግሞ ከተወለዱ በኋላ የልብ በሽተኛ ይሆናሉ። ሕክምናውን ስለማያገኙ ደግሞ ይሞታሉ" ይላሉ።

ዶ/ር በላይ አበጋዝ ከ1973 ዓ.ም ጀምረው ላለፉት 41 ዓመታት በሕጻናት ሕክምና እና በሕጻናት ካርዲዮሎጂስትነት በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር በሙያቸው አገልግለዋል። ከሕክምናው በተጨማሪም የሕጻናት ሕክምና ሳይንስን (ፔዲያትሪክስን) አስተምረዋል፣ ስለ ሙያውም ልዩ ልዩ ጥናታዊ ጽሑፎችን አሳትመዋል። በተጨማሪም በተለያዩ አካዳሚዎች ውስጥ ተሣትፎ በማድረግ ይታወቃሉ።

ከነዚህም ውስጥ ከ1981 ዓ.ም ጀምረው የአሜሪካ ፔዲያትሪክስ አካዳሚ በአባልነት፣ በInternational Society of Hypertension in Blacks በአባልነት፣ በThe Pan African Society of Cardiology በአባልነት፣ The National Drug Advisory Board of Ethiopia አባል ሲሆኑ፣ በEthiopian Medical Journal በአባልነት፣ በረዳት ዋና ፀሐፊነትና በሊቀ መንበርነት አገልግለዋል፡፡ የHealing the Children USA, Save a Child's Heart ISREAL and Chain of Hope UK ተባባሪ ናቸው። የአዲስ አበባ ላየንስ ክለብ አባል እና ዋና አራማጅም ናቸው።

ዶክተር በላይ አበጋዝ ለበርካታ ዓመታት ደከመኝ ሠለቸኝ ሳይሉ በወቅቱ የሚያጋጥማቸው መሰናክሎችና ችግሮች ሳይበግራቸው ለሀገራቸው በሕክምናው ዘርፍ የማይረሳ ዐሻራ አሳርፈዋል። በዚህም ምክንያት በሀገር ውስጥ እንዲሁም ከሀገር ውጭ በርካታ ሽልማቶችን ያገኙ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ በ2008 ዓ/ም በልብ ሕክምና ዘርፍ ባደረጉት በጎ አስተዋጽኦ ከወሎ ዩኒቨርሲቲ የክብር ዶክትሬት ማዕረግ ተቀብለዋል።

በ2006 ዓ.ም የበጎ ሰው ሽልማት ተሸላሚ ነበሩ፤ የልብ ሕሙማን ሕክምና መርጃ ማህበር ምስረታ 30ኛ ዓመት ሲከበርም ከጠቅላይ ሚንስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር) እጅ የሕይወት ዘመን አገልግሎት ሜዳልያ ዕውቅና ሽልማት ተበርክቶላቸዋል። በአሁኑ ወቅት የብሩክ የሕክምና አገልግሎቶች ድርጅት በሙሉ ጊዜያቸው በግላቸው እየሰሩ ይገኛሉ። እሳቸው የመሠረቱት የኢትዮጵያ የልብ ሕክምና ማዕከል በርካታ ሕጻናትን ጨምሮ በኢትዮጵያ የልብ ሕክምና በስፋት እንዲሰጥ የሳቸው ዐሻራ ዘመን ተሻጋሪ ነው።

ሕክምና የሚያስፈልጋቸው ሕፃናት ወደ ውጭ ሀገራት ሄደው በቋንቋ ከማይመስሏቸው በመልክ ከማይመስሏቸው ውሃ ብለው ቢጠይቁ ውሃ ምን እንደሆነ በማያውቁ ነርሶችና ሐኪሞች መታከሙ እራሱን የቻለ በደል በልጆች ላይም የሚያሳድረው የአእምሮ ጠባሳ ቀላል እንዳልሆነ የሚናገሩት ዶክተር በላይ በራስ ወገን የልጆቹም ወላጆች ባሉበት መታከም መቻሉ ፋይዳው ትልቅ በመሆኑ እንደ ቀላል የሚታይ ስላለመሆኑ ይናገራሉ።

ከዛሬ 14 ዓመት በፊት የተቋቋመው የሕፃናት የልብ ሕክምና ማዕከል በኢትዮጵያውያን ሐኪሞች ከባድ ሊባሉ የሚችሉ የልብ ቀዶ ጥገና በሀገር ውስጥ መስጠት መቻሉ የሚናገሩት ዶክተር በላይ ነገር ግን በአላቂ ዕቃዎች ዕጥረት የተነሳ ሆስፒታሉ የተሟላ አገልግሎት መስጠት አለመቻሉ የሚያስቆጫቸው ስለመሆኑ በተደጋጋሚ ይናገራሉ።

ዶክተር በላይ በተለይ በአላቂ ዕቃዎች ዕጥረት ምክንያት ቀዶ ሕክምና ማድረግ እያለባቸው ሕክምና ማግኘት ያልቻሉ ሮጠው ያልጠገቡ ሕፃናት ሕይወት እንዳይጠፋ መንግሥት ድጋፍ ሊያደርግ እንደሚገባ በማንሳት ከዚህም ባሻገር ማዕከሉ ጠንክሮና በሁለት እግሩ ቆሞ ለብዙዎች መድረስ እንዲችል ሁሉም ኢትዮጵያዊ ከጎኑ መቆም እንዳለበት ይናገራሉ።

ቀደም ባሉት ዓመታት የልብ ሕመም የሰለጠኑ ወይም የሀብታም ሀገራት የጤና ችግር ብቻ ተደርጎ ይታሰብ ነበር። ይሁን እንጂ ችግሩ በማደግ ላይ ያሉ ወይም የደሃ ሀገራትም ዋነኛ አሳሳቢ ፈተና መሆኑ አልቀረም። ከዚህ ቀደም በበለፀጉ ሀገራት ሕዝቦች ዘንድ በስፋት ይታይ የነበረው የልብ ሕመም እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ታዳጊ ሀገራት ሕዝቦች ላይም የተጋረጠ ፈተና መሆነ በጉልህ እየታየ ይገኛል።

የልብ ቀዶ ጥገና በኢትዮጵያውያን የሕክምና ባለሙያዎች መሰጠት በጀመረ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ በየዓመቱ እስከ መቶ የሚደርሱ የልብ ታማሚዎች በሀገር ውስጥ ያለ ምንም ወጪ ይታከማሉ። ይሁን እንጂ አሁንም በኢትዮጵያ የልብ ቀዶ ሕክምና ለማድረግ ቁጥራቸው ቀላል የማይሆኑ ሕፃናት ወረፋ በመጠባበቅ ሕክምናቸውን በጊዜ ለማግኘት እንደሚቸገሩ የኢትዮጵያ የልብ ሕሙማን ሕጻናት መርጃ ማዕከል ይገልፃል። በየዓመቱ እስከ 500 የሚደርሱ ሕጻናት የልብ ቀዶ ሕክምና እየተደረገላቸው እንደሚገኝ እና ቀዶ ሕክምና የሚፈልጉ ሕጻናት ቁጥር በየቀኑ እንደሚጨምር ማዕከሉ ያስረዳል።

በማዕከሉ አላቂ እቃዎች በበቂ ሁኔታ ባለመኖራቸው የተነሳ ወረፋ የሚጠብቁ ሕጻናት ሕክምና እያገኙ አለመሆናቸውን እና መድኃኒትም ቢሆን በሚፈለገው መጠን አለመገኘቱ በሥራው ላይ እንቅፋት እንደሆነበት በተደጋጋሚ የሚገልጸው ተቋሙ፤ አላቂ እቃዎች እና መድኃኒቶች በበቂ መጠን ቢያሟሉ ኖሮ ግን በዓመት ከ 1 ሺህ 500 ያላነሰ ቀዶ ጥገና ማድረግ ይቻል እንደነበር ያስረዳል።

እኛም በእኚህ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ምሁር የተመሠረተውን ይህንን የነገ ሀገር ተረካቢ ሕፃናት ተስፋ የሆነውን ተቋም ሁሉም ኢትዮጵያዊ በሚችለው ሁሉ ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅበታል እያልን ለማዕከሉ መስራች ዶክተር በላይ አበጋዝ ረጅም ዕድሜ ከጤና ጋር ፈጣሪ እንዲሰጣቸው እንመኛለን።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

# አዲስ ዘመን ረቡዕ ስፖርት

ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

## ዓለም አቀፍ የታዳጊዎች የቴኒስ ውድድር በኢትዮጵያ እየተካሄደ ነው

ዓለማየሁ ግዛው

በኢትዮጵያ አስተናጋጅነት እየተካሄደ በሚገኘው ዓለም አቀፍ የወጣቶች የሜዳ ቴኒስ ውድድር ኢትዮጵያውያን የቴኒስ ተወዳዳሪዎች ጥሩ እንቅስቃሴን እያደረጉ ነው። በውድድሩ ከ24 የዓለም ሀገራት የተወጣጡ ከ45 በላይ የሚሆኑ እድሜያቸው ከ13 እስከ 18 ዓመት የቴኒስ ተወዳዳሪዎች እየተሳተፉ ይገኛሉ።

በሁለት ዙሮች የሚጠናቀቅ «ኢንተርናሽናል ጁኒየር (J-30) አዲስ አበባ» የተሰኘ የወጣቶች የሜዳ ቴኒስ ውድድርን በማስተናገድ ላይ ትገኛለች። ተመሳሳይ ውድድር በኢትዮጵያ ሲዘጋጅ በአጠቃላይ ለሦስተኛ ጊዜ ሲሆን በወጣቶች መካከል ሲዘጋጅ ደግሞ ሁለተኛው ነው። የመጀመሪያው ዙር ውድድር ከኅዳር 15 ጀምሮ በአዲስ አበባ ቴኒስ ክለብ የተካሄደ ሲሆን ከቀናት በፊት ተጠናቋል። ሁለተኛው ዙር ውድድርም እየተካሄደ የሚገኝ ሲሆን ኅዳር 30-2016 ዓ.ም እንደሚጠናቀቅ ለማወቅ ተችሏል። ውድድሩን የኢትዮጵያ ቴኒስ ፌዴሬሽን ከዓለም አቀፉ ቴኒስ ፌዴሬሽን የተሰጠውን እድል ተጠቅሞ ከአዲስ አበባ ቴኒስ ክለብ ጋር በመተባበር ማዘጋጀቱም ተጠቁሟል።

በዚህ ወድድርም ከ5 መቶ እስከ 1ሺ ዓለም አቀፍ የቴኒስ ደረጃ ያላቸው ወጣት ተወዳዳሪዎች እየተሳተፉ ይገኛሉ። ከዚህ ደረጃ ዝቅ ያሉት ተወዳዳሪዎች ውድድሩን መካፈል የማይችሉ ሲሆን እንደዚህ አይነት ውድድሮችን ለመሳተፍ እያንዳንዷ ነጥብ ያላት ዋጋ ከፍተኛ ነው። በሁለቱም ፆታዎች እየተካሄደ በሚገኘው ውድድር ኢትዮጵያ በ5 ሴትና በ5 ወንድ በጥቅሉ በ10 ተወዳዳሪዎች ተወክላ ተስፋ ሰጪ የሆነ እቅስቃሴን በማድረግ ላይ እንደምትገኝ የኢትዮጵያ ቴኒስ ፌዴሬሽን አስታውቋል። በውድድሩ ጠንካራ እንቅስቃሴ እየተደረገበት ሲሆን ኢትዮጵያውያን ተጫዋቾች ከዚህ በፊት ከነበሩት ውድድሮች የተሻለ እንቅስቃሴና ጠንካራ ፉክክር ማሳየት ችለዋል።


ውድድሩ ለታዳጊ ኢትዮጵያውያን የዓለም አቀፍ ውድድር እድል ይፈጥራል፣

ከ24 የዓለም ሀገራት የተወጣጡ ቁጥራቸው ከ45 በላይ የሆኑ ድንቅ ተሰጥዖ ያላቸው ከ13 እስከ 18 ዓመት የሆኑ ታዳጊዎች በሚፋለሙበት ውድድር ኢትዮጵያውያን ተወዳዳሪዎች ውጤት ባይቀናቸውም ጠንካራ ፉክክር ማድረግ ችለዋል። ከዚህ በፊት በነበሩት ውድድሮች ሁለት በሴት እና ሁለት በወንድ ተጫዋቾች በአጠቃላይ በአራት ኢትዮጵያውያን ተወዳዳሪዎች ዓለም አቀፍ ደረጃን ማግኘት ተችሏል። በተጠናቀቀው የመጀመሪያ ዙር ውድድር በሁለቱም ፆታ አራት ተወዳዳሪዎች ቀጣዩን ዙር በመቀላቀል ተፎካካሪ ቢሆኑም ከዚያ በላይ መጓዝ ግን አልቻሉም።

ዓለማቀፉ የቴኒስ ፌዴሬሽን ለውድድሩ የሚያደርገው የገንዘብ ድጋፍ እንደሌለ ፌዴሬሽኑ የገለፀ ሲሆን፤ የተጫዋቾች ምዝገባ እና የውድድሩን ጥራት የመቆጣጠር በርካታ ሥራዎችን ሠርቷል። ፌዴሬሽኑ ለውድድሩ በራሱ ወጪ የውድድር አማካሪ ከውጪ በማስመጣት ውድድሩን እያካሄደ እንደሚገኝም አስታውቋል። ውድድሩን ከስፖንሰር በሚገኝ ገንዘብ አማካኝነት እያካሄደ እንደሆነና ዓለም አቀፉ ተቋም ሙያዊ ድጋፎችን ብቻ እንደሚያደርግለትም ጠቁሟል።

የወጣቶች ወድድር ላይ የገንዘብ ሽልማት የማይፈቀድ በመሆኑ በውድድሩ የሚያሸንፉ ተወዳዳሪዎች 30 ነጥብ የሚያገኙ ይሆናል። አሸናፊዎቹ ተወዳዳሪዎች የሚያገኙት ነጥብ ከዚህ በፊት ባላቸው ነጥብ ላይ የሚደመርላቸው ሲሆን በዓለም ላይ ያላቸውን ደረጃ ይጨምርላቸዋል። ተጫዋቾቹ ዓለም ላይ ያላቸው ደረጃም በየትኛውም ዓለም አቀፍ ውድድር ቅድሚያ የመወዳደር እድል ስለሚሰጣቸው ጠንካራ ፉክክር ያደርጋሉ።

በመጠናቀቅ ላይ እስካለው የፈረንጆቹ ዓመት ድረስ ነጥብ ማግኘት የቻለ አንድም ኢትዮጵያዊ ተወዳዳሪ አለመኖሩ የተገለጸ ሲሆን፤ ኢትዮጵያ ይሀን ውድድር በማስተናገዷ ግን ኢትዮጵያውያን ነጥብ ማግኘት ችለዋል። በዚህም በተገኘው ነጥብ ዓለም አቀፍ ደረጃ ውስጥ መግባት በመቻላቸው የኢትዮጵያ ስም በዓለም የቴኒስ ደረጃ ውስጥ ከሰፈሩ ሀገራት አንዷ እንድትሆን ማስቻሉ ተጠቅሷል። በዚህም ውድድር በመጀመሪያው ዙር ውጤት ባይቀናቸውም ያሳዩት እንቅስቃሴ በሁለተኛው ዙር እንዲጠበቁ አድርጓልም።

የኢትዮጵያ ቴኒስ ፌዴሬሽን የሥራ አስፈጻሚ አባል አቶ ሚካኤል ንጉሤ፤ ኢትዮጵያ ውድድሩን በተደጋጋሚ ማዘጋጀቷ ለኢትዮጵያውያን ተወዳዳሪዎች የሚያወጡትን ከፍተኛ ወጪ እንደሚያስቀርላቸው አስረድቷል። ስፖርተኞቹ ጥሩ የሚባል የቴክኒክ ብቃት ያላቸው ቢሆንም ውድድር የማያገኙ በመሆኑ ያንን በመቅረፍ የራስ መተማመንን እንዲያጎለብቱ ሊረዳ እንደቻለም ገልጸዋል። ዓለም አቀፍ ውድድሮች በበዙ ቁጥር ለውድድሩ የሚያስፈልጉ መሠረተ ልማቶች እንዲሟሉም ይረዳል። ለስፖርቱ የሚመደበው በጀት ጥቂት በመሆኑ እና የሀገር ውስጥ ውድድሮች ባለመስፋፋታቸው እንደዚህ ዓይነት ዓለማቀፍ ውድድሮች መፈጠራቸው የሀገር አቀፍ ውድድሮችን ለማነቃቃትና ስፖርቱን ለማሳደግ ትልቅ ጠቀሜታ ይኖረዋል። በተጨማሪም ኢትዮጵያውያን ወጣቶች እያደረጉ የሚገኙት እንቅስቃሴ ተስፋ ሰጪ በመሆኑ በቀጣይ ባሉት ውድድሮች በጉጉት እንዲጠበቁ ማድረጉንም ተናግረዋል።

ውድድሩን በበላይነት የሚያስተዳድረው ዓለም አቀፉ የቴኒስ ፌዴሬሽን፤ የቴኒስ ስፖርትን ከሚያሳድግባቸው ዋንኞቹ ተግባራት ውስጥ የወጣቶች ውድድር አንዱ ነው። በዚህም የኢትዮጵያ ቴኒስ ፌዴሬሽን ለመደገፍና ስፖርቱን ለማሳደግ እንዲህ ዓይነት ውድድሮችን የማዘጋጀት ፍቃድ ይሰጣል። ለአንድ ጀማሪ ሀገር በአንድ ዓመት የማዘጋጀት እድሉ ሁለት ጊዜ ብቻ ቢፈቀድም፤ ኢትዮጵያ በከዚህ ቀደሞቹ ውድድሮችን በጥሩ መንገድ ስላስተናገደች ለሦስተኛ ጊዜ የማዘጋጀት እድሉን ልታገኝ እንደቻለችም ተጠቁሟል።

ከዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

## የዩኒቨርሲቲው ስኬት - በዓለም አቀፋዊ አጋርነት

ዳንኤል ዘነበ

በአሁኑ ወቅት ዓለም ግሎባላይዜሽን (ሉላዊነት) በምንለው ሥርዓት ውስጥ ትገኛለች። በዚህ የግሎባላይዜሽን ሥርዓት ውስጥ በማንኛውም መስክ ከፍተኛ ትምህርት ላይ የሚታዩና ሰፋፊ የሆኑ እንቅስቃሴዎች አሉ። ለምሳሌ የመምህራንና የተማሪዎችን ንቅናቄ ብንወስድ ተማሪዎች ከአንድ አኅጉር ወደ ሌላ አኅጉር እየሄዱ የሚማሩበት፤ እንዲሁም መምህራን ከአንዱ አኅጉር ወደ ሌላው አኅጉር በመሄድ የሚሠሩበት ሁኔታ አለ። በምርምርም በኩል ሲታይ እንደዚሁ ተቋማት ብቻቸውን ብቻ ሳይሆን ከሌሎች ተቋማት ጋር በመነጋገርና አብረው በመሆን የግል፣ የጋራ፣ የአካባቢና የሀገራት ችግሮችን የሚፈቱበት የትብብር መስክ አለ። ከእነዚህ የትብብር መስኮች በተለምዶ አባባል ኢንተርናላይዜሽን ወይም ዓለም አቀፋዊነት የምንለውን ዘርፍ አቅፈዋል ።

ተቋማትም ለዚህ ዓይነቱ ዓለም አቀፋዊ ንቅናቄ ራሳቸውን ማዘጋጀት ይገባቸዋል። በተለይ በምርምር ዙሪያ በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ላይ ተቋማት ከሌሎች ተቋማት ጋር የሚያደርጉት ተሳትፎ፣ እርስ በርስ ያለ ግንኙነት ወሳኝ ነው ። ዩኒቨርሲቲዎች ዛሬ የሚያዘጋጇቸው ተማሪዎች የሀገሪቷ ዜጎች ብቻ ሳይሆኑ ዓለም አቀፋዊ ባህሪ ያላቸው፣ የትም ቦታ ሄደው መሥራት የሚችሉ፣ ሊሆኑ ይገባል ተብሎ ይታመናል። ይህም በሀገራችን የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች “ኢንተርናላይዜሽንና ፓርትነርሺፕ” በስትራቴጂክ እቅዳቸው ውስጥ አካተው መሄድ እንዳለባቸው ይጠቁማል ።

ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲም የማኅበረሰብ ተጠቃሚነትን


አቶ ዳንኤል ገዴ የሕዝብ ግንኙነትና ዓለም አቀፍ ጉዳዮች ዳይሬክተር፤

ለማረጋገጥ እንዲሁም ያስቀመጥነውን ራዕይ ዕውን ለማድረግ በዓለም አቀፍ ደረጃ ስመጥር ከሆኑ አቻ ተቋማት ጋር አብሮ እየሠራ ይገኛል። አቶ ዳንኤል ገዴ በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ የሕዝብ ግንኙነትና ዓለም ዓቀፍ ጉዳዮች ዳይሬክተር ናቸው ።

አቶ ዳንኤል እንደሚገልጹት፤ ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ በተለያዩ ሀገራት ከሚገኙት ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በትብብር ለመሥራት የጋራ የስምምነት ውል ከመፈራረም ጀምሮ የተቋሙን ራዕይ ለማሳካት ሰፊ እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል። ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ዩኒቨርሲቲው በትኩረት አቅጣጫዎች መሠረት ከሌሎች ተቋማት ጋር አብሮ እየሠራ ነው ። ከዚህም ቀደም ሲል በሀገረ ጀርመን ከሚገኘው የቤርልን አፕላይድ ሳይንስ ዩኒቨርሲቲ ጋር በጋራ ለመሥራት መስማማታቸውን አስታውቀዋል ።

በዚህ መሠረት እ.ኤ.አ ከ2023 ጀምሮ በተለይም በኢንጂነሪንግና ቴክኖሎጂ እንዲሁም በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ዘርፎች በጋራ ለመሥራት በመስማማት ከዩኒቨርሲቲው ጋር አብሮ እየሠራ ነው የሚሉት አቶ ዳንኤል፣ “በሁለቱ ዩኒቨርሲቲዎች መካከል የተደረገው የጋራ ስምምነት የዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ሀብታሙ አበበ በጀርመን ሀገር የሚገኘውን የቤርሊኒ አፕላይድ ሳይንስን ከጎበኙ በኋላ ነው” ብለዋል ።

አቶ ዳንኤል፤ የሁለትዮሽ ስምምነቱ በመፈረሙ የተገኘውን ውጤት በተመለከተ ሲያስረዱ፣ የአይሲቲ መሠረተ ልማት እንዲዘረጋ ማድረግ የተቻለ ሲሆን፣ ይህም የቴክኖሎጂ ዘርፍ ተማሪዎች ትምህርታቸውን አጠናቀው ሲወጡ የአገሪቱን የቴክኖሎጂ ችግር ለመፍታት የሚያስችል አቅም ይዘው እንዲወጡና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ከድርጅቱ ጋር ትስስር ፈጥሮ እየሠራ መሆኑን አመልክተዋል። የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች በቴክኖሎጂው ዘርፍ ያላቸውን እውቀት እንዲያሳድጉ እና በሀገር አቀፍ ራሳቸውን ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ታሳቢ በማድረግ ነው ። እንደ ሀገር የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እንዲያድግ በማድረግ ትልቅ ጥቅም ይኖረዋል።

ዩኒቨርሲቲው በቀጣይም በትኩረት አቅጣጫዎች መሠረት ከሌሎች ተቋማት ጋር አብሮ ለመሥራት በሚያስችሉ ጉዳዮች ዙሪያ የሚሠራ መሆኑንም የገለጹት አቶ ዳንኤል፣ በዚሁ መሠረት ከሰሞኑ ዩኒቨርሲቲው ከአሌክሳንደሩ አይኦና ሱዛ ዩኒቨርሲቲ በተመረጡ የሥራ መስኮች ዙሪያ በጋራ ለመሥራት በሚያስችሉ ጉዳዮች ዙሪያ ውይይት መደረጉን አስታውቀዋል ። ከአሌክሳንደሩ አይኦና ሱዛ ዩኒቨርሲቲ ምክትል ፕሬዚዳንት ጊና መርኔስኩ ጋር በበይነ መረብ የተደረገ መሆኑን ጠቅሰው፤ በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ በኩል በፕሬዚዳንት ጽሕፈት ቤት ስር የሚገኘው የልህቀት ማዕከላት እና የትብብር ፕሮጀክቶች ዳይሬክቶሬት ዶክተር አዳነ ወልደመድን እና የሕዝብ ግንኙነትና ዓለም አቀፍ ጉዳዮች ዳይሬክተር ተሳታፊ መሆናቸውን ገልጸዋል።

ዩኒቨርሲቲዎቹ በቀጣይ በሚሠሩት ሥራ ዙሪያ በስፋት ውይይቱ ተደርጓል። ሁለቱ ዩኒቨርሲቲዎች የአካዳሚክ ስታፍ ልውውጥ፣ የሁለትዮሽ የጋራ ሳይንሳዊ ምርምር ፕሮጀክቶች እና የሦስተኛ ዲግሪ ፕሮግራም ላይ በጋራ ለመሥራት የሚያስችል ውጤታማ ውይይት አካሂደዋል። በውይይቱ መሠረት በቀጣይ የሁለቱንም ተቋማት ጠንካራ ግንኙነት ይበልጥ ለማጠናከር እና ወደ ውጤት ለመቀየር እንደሚሠራ ገልጸዋል። በተለይም በማኅበራዊ ሳይንስ፣ በተፈጥሮ ሳይንስ፣ በትምህርት እና ሥነ ባሕሪ እንዲሁም ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ የትምህርት መስኮች በልዩ ትኩረት እንደሚሠራም ነው አቶ ዳንኤል ማብራሪያ የሰጡት ።

በአጠቃላይ ዩኒቨርሲቲው በሁለትዮሽ አጋርነት ለሚተገበሩ የዓለም አቀፋዊነት ሥራዎች ልዩ ትኩረት ሰጥቶ በተቀናጀ መልኩ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። እንደ ተቋም በዓለም አቀፋዊነት የትብብርና የአጋርነት ማዕቀፍ በርካታ የመግባቢያ ሰነዶችን በመፈራረም ወደ ሥራ መግባት ችሏል። ይህም ዩኒቨርሲቲው በተለያዩ የሥራ መስኮች ከዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር በትብብርና አጋርነት ለመሥራት መፈራረሙ ለተቋሙ የዕድገት ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል። ዩኒቨርሲቲው በቀጣይ የተቋሙን ተልዕኮ እና የትኩረት መስክ ታሳቢ ባደረገ መልኩ ከዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር አጋርነት በመመስረት ሀብት የማፈላለግ ሥራ ላይ ትኩረት ሰጥቶ እንደሚሠራ ይጠበቃል ።

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ